# ተፈሪ ማርሽ፣ ማኅበረ-ታሪካዊ ዐውድ ትርጉምና ትንተና

መስፍን መሰለ[1]

## አኅጽሮተ ጥናት

ለመጀመሪያ ጊዜ በ1917 ዓ. ም. የተዘመረው ተፈሪ ማርሽ ለብዙ ዓመታት በትምህርት ቤቶችና በሌሎችም አጋጣሚዎች ላይ ተዘምሯል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር አገልግሎት መስጠት ከጀመረ በኋላም አገልግሎቱ አልተቋረጠም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር በሚቀርብበት አጋጣሚ ላይ ቀድሞ ወይም ዘግይቶ ይዘመር ነበር፡፡ አንዳንድ ጊዜም የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙርን ሚና ይተካል፡፡ ይኹን እንጂ፣ ይኽንን መዝሙር በተመለከተ በአጥኚዎች የተዘገበው፣ አንድም የተሳሳተ ነው፡፡ አንድም፣ መዝሙሩን ከመመዝገብ በስተቀር ጥናት አልተካኼደም፡፡ የዚኽ ጥናት ዓላማም የተሳሳተውን ጥናት በመጥቀስ ትክክለኛውን ማሳየት፣ በመዝሙሩ የተንፀባረቀውን መመርመር፣ መተርጎምና መተንተን ነው፡፡ በመዝሙሩ ምን ምን ተንጸባረቀ? በመዝሙሩ የተንጸባረቀው ምን ያኽል ታሪካዊ እውነታውን ይገልጻል? ለሚሉት ጥያቄዎች ጥናቱ መልስ ይሰጣል፡፡ ጥናቱ ትኩረት ያደረገበት ተፈሪ ማርሽ የትምህርትና ሥነጥበብ ሚኒስቴር (፲፱፻፳፬) ካዘጋጀው መጽሐፍ የተወሰደ ነው፡፡ መዝሙሩ የተተረጎመውና የተተነተነው የተዘመረበትን ማኅበራዊ፣ ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ዐውዶች መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ለጥናቱ የሚረዱ ተጨማሪ መረጃዎች ከጋዜጦች፣ ከመጻሕፍትና ከምርምር ውጤቶች ተሰብስበው በማገናዘቢያነት አገልግለዋል፡፡ ከጥናቱ ውጤት መረዳት እንደሚቻለው መዝሙሩ በአራት ጉዳዮች ላይ ያተኩራል፡፡ አንደኛው፣ ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ለኢትዮጵያ ሕዝብ የፈጸሟቸውን ተግባሮች በማውሳት ያሞግሳል፤ ለአፍሪካ ሕዝብም የተስፋ ብርሃን መኾናቸውን ያንፀባርቃል፡፡ ኹለተኛ፣ ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና ነጻነት ያስከብራሉ፣ ይጠብቃሉ የሚል እምነትን ያስተጋባል፡፡ ሦስተኛ፣ ከፈጣሪ የተሰጣቸውን ጥበብ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያወርሳሉ ተብሎ ተስፋ መደረጉን ያንፀባርቃል፡፡ አራተኛ፣ የልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ዕድሜ እንዲረዝም፣ ሺሕ ዓመት እንዲኖሩ፣ ሕያው እንዲኾኑ ይመኛል፤ ለፈጣሪ ተማጽእኖ ያቀርባል፡፡ በመዝሙሩ የተንጸባረቁትን አራት ጉዳዮች በትውልዱ ለማስረጽም ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በሚገኙባቸው አጋጣሚዎች (ዝግጅቶች) ኹሉ ይዘመራል፡፡ ተፈሪ ማርሽ የልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንን ማንነት መገንቢያ መሣሪያ ኾኖ አገልግሏል፡፡ ይኽ ጥናት ሥጋዊ ጉዳይ ላይ የሚያተኩር መዝሙር በዐማርኛ ቋንቋ ማቅረብ የተጀመረበትን ለመገንዘብ ያስችላል፡፡ በዐማርኛ መዝሙር ታሪክ ሊኖረን የሚገባውን ዕውቀት ያሰፋል፡፡ በመዝሙሩ የተንጸባረቀውን ታሪካዊ ዕውነታ ያስረዳል፡፡ የመዝሙሩ አገልሎት በሕግ ባለመደንገጉ የሚዘመርባቸውን አጋጣሚዎች ጠንቅቆ ለማወቅ አልተቻለም፡፡ እንደዚኹም፣ ከ1920 ዓ. ም. ጀምሮ አልግሎት ይሰጥ ከነበረው የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር ጋር የነበረውን የአገልግሎ ልዩነትና አንድነት ማስረዳት አልተቻለም፡፡ እነዚኽን ክፍተቶች ለመሙላት ተጨማሪ ጥናት ማካኼድ አስፈላጊ ነው፡፡

**ቁልፍ ቃላት፡-** [ተፈሪ ማርሽ፣  ሙገሳ፣ ምርቃት]

---

[1] በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ የፎክሎና ሥነጽሑፍ ተመራማሪ ፡፡

## 1) መግቢያ

መዝሙር የመድረስና የማቀነባበር ሥራ ቀጣይነት ባለው መንገድ የተጀመረው በ1917 ዓ. ም. ነው፡፡ ይኸንንም ዮሐንስ (፪ሺህ፬፤ 44) "ዘመናዊ የመዝሙር ድርሰት መዘመር የጀመረው የተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ከተቋቋመና ሥራ ከጀመረ ከ1917 ዓ. ም. ከሚያዝያ 19 ወዲህ ነው፡፡ ይህ አዲሱ ዘመን ያስገኘው የመዝሙር አደራረስ ስልት ቀስ በቀስ እየተለመደ፣ በየትምህርት ቤቱ እየተዛመተ ተወዳጅ ኪን ሆነ፡፡" በማለት ገልጸውታል፡፡ ተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት በተከፈተበት ዕለት የተዘመረውን የመጀመሪያው መዝሙር ያቀነባበረው ኪቮርክ ናልባንዲያን[2] ሲኾን መዝሙሩም ማርሽ ተፈሪ ነው፡፡ ዘማሪዎቹም መስከረም 16 ቀን 1917 ዓ. ም. አዲስ አበባ የገቡት አርባው የአርመን ልጆችና ማዘጋጃ ቤት ሙዚቃ እንዲማሩ የመረጣቸው ኢትዮጵያውያን ልጆች ናቸው፡፡ መዝሙሩን ያስጠናቸው የሙዚቃ መምህሩ "ሙሴ ኬቦርክ ናልባንዲያን" ነበር (መርስዔ ኀዘን፣ 1999፤ 279፣ 282)፡፡ ይኸ መዝሙር ተማሪ ቤቱ በተከፈተበት ዕለት የተዘመረው ቃሉ ተማሪ ቤቱ ከመከፈቱ በፊት ተደርሶ፣ በዜማ ተቀነባብሮና በዘማሪዎቹ ተጠንቶ ነው፡፡ ይኸ መዝሙር ከተዘመረ ከሦስት ወር በኋላ "የኢትዮጵያን ብርሃን" የሚባለው የተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት መዝሙር ተዘመረ፡፡[3] በተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት የተጀመረው መዝሙርን በዜማ የማቀነባበርና በተማሪዎች የማዘመር ሥራ በዳግማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤትም እንዲለመድና መነቃቃት እንዲፈጠር ረድቷል (መርስዔ ኀዘን፣ 1999)፡፡

ከ1917 ዓ. ም. ጀምሮ ኢጣሊያ ኢትዮጵያን እስከ ወረረችበት 1928 ዓ. ም. ድረስ የተለያየ ይዘት ያላቸውን መዝሙሮች በዜማ የማቀነባበር ሥራ በተማሪ ቤቶች ሲከናወን ቆዬ፡፡ በኢጣሊያ ወረራ ምክንያት ተቋርጦ ቢቆይም ኢትዮጵያ ነጻ ከወጣች ከ1933 ዓ. ም. በኋላ መዝሙርን ማቀነባበርና በተማሪ ቤት የማዘመሩ ሥራ ተጠናክሮ ቀጠለ፡፡ በርካታ መዝሙሮችም በተለያዩ ሰዎች እየተደረሱና በዜማ እየተቀነባበሩ በትምህርት ቤቶች አገልግሎት እንዲሰጡ ተደረገ (ከታኅሣሥ 23 ቀን 1917 ዓ. ም. ጀምሮ የታተሙ "ብርሃንና ሰላም" ጋዜጣ፤ መርስዔ ኀዘን፣ 1999፤ ዮሐንስ፣ ፪ሺህ፬)፡፡ መዝሙር እየደረሱ በተማሪ ቤቶችና በወጣቶች ማዘመር እንደ ባሕል ተቆጠረ፡፡ በኪቮርክ ናልባንዲያን የተጀመረው መዝሙርን የማቀነባበር ሥራ በወንድማቸው ልጅ በነርሲስ ናልባንዲያን (Nalbandian, 2020) እና በኢትዮጵያውያን ቀጠለ፡፡

በ1964 ዓ. ም. ትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር "የተማሪ ቤት መዝሙር" በሚል ርእስ 22 መዝሙሮችን በየተማሪ ቤቱ እንዲዘመሩ በመጽሐፍ አትሞ አቀረበ፡፡ በመቅድሙም

[2]አርባው የአርመን ልጆችና የሙዚቃ አስተማሪያቸው ኪቮርክ ናልባንዲያን አዲስ አበባ የመጡት በልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ጋባዥነት ነው (Nalbandian, 2019)፡፡ በማዘጋጃ ቤት ወጣቶችን ሙዚቃ በማሰልጠን ሥራቸውን የጀመሩት ኪቮርክ ናልባንዲያን፣ ከ1917 ዓ. ም. አጋማሽ በኋላ በተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት የሙዚቃ አስተማሪ ኾነው ተቀጠሩ (የተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት አጭር ታሪክ፣ ፲፱፻፵)፡፡ እሳቸውም መዝሙሮችን በማቀነባበር በተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤትና ከተማሪ ቤቱ ውጭ በተማሪዎች እንዲዘመሩ በማድረግ በአማርኛ የመዝሙርን ባሕል ለኢትዮጵያውያን አስተዋወቁ፡፡ ካቀነባበሯቸው በርካታ መዝሙሮች መካከል "ተፈሪ ማርሽ"፣ "ኢትዮጵያ ሆይ" (የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር) እና "የሰንደቅ ዓላማ የክብር ሰላምታ መዝሙሮች" በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

[3]መጀመሮ[ሪያ] ዓመት፣ ቁጥር ፴፩፣ ኀሙስ ሐምሌ ፳፫ ቀን ፲፱፻፲፯፡፡

እንደተገለጸው በመጽሐፉ የሚገኙት መዝሙሮች በተማሪዎቹ ወላጆች በተማሪ ቤቶች ለብዙ ዓመታት ሲዘመሩ እንደ ነበር ተገልጿል፡፡ መዝሙሮቹ በመጽሐፉ የታተሙበት ምክንያት በጊዜ ብዛት እንዳይረሱና በወጣቱ አንደበት እየተዜሙ ሕያው ሆነው እንዲኖሩ በማሰብ ነው፡፡ የተማሪ ቤት መዝሙሮቹ ስለ ዐድዋ ድል፣ ስለ ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን (በኋላ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ)፣ ስለ ሀገር ፍቅር፣ ስለ ሰንደቅ ዓላማ ክብርና ስለ ቀለማቱ ተምሳሌትነት፣ ስለ ታሪክ፣ ስለ ጀግንነት፣ ስለ መተባበር፣ ስለ መንፈሳዊ ሕይወት፣ ስለ ሀገር ዕድገት፣ ወዘተርፈ የሚያወሱ ናቸው፡፡ በመዝሙሮቹ የተንጸባረቀው ይዘትም በወጣቱ ዘንድ ሥጋዊና መንፈሳዊ ሕይወትን ለማስረጽ ይደረግ የነበረውን ጥረት ያስረዳሉ፡፡ ይኹን እንጂ፣ በትምህርት ቤት እንዲዘመሩ በተዘጋጁት መዝሙሮች ላይ ትኩረት በማድረግ ጥናት አልተደረገም፡፡ "መንግሥት እንደ ዳዊት" የሚለውን መዝሙር "ተፈሪ ማርሽ ነው" ብለው የገለጹ፣ እንዲኹም መዝሙሩን ከሌላ ሥራቸው ጋር የመዘገቡ አሉ፡፡ ስለኾነም፣ ስሕተቱን በማረምና ትክክለኛውን መዝሙር መግለጽ በተለያዩ ሥራዎች የተመዘገበውን መመርመርና መተንተን አስፈላጊ ኾኗል፡፡

የዚኽ ጥናት ዓላማ የተለያዩ መዝሙሮችን ሰብስብ በያዘውና በትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር በታተመው መጽሐፍ "ተፈሪ ማርሽ" በሚል ርእስ በተመዘገበው መዝሙር የተንፀባረቀውን ማኅበረ-ታሪካዊ ዐውድ መሠረት በማድረግ መተርጎምና መተንተን ነው፡፡ ከዚኽ ዋና ዓላማ የሚመነጩ ንዑስ ዓላማዎችም፣ 1) በመዝሙሩ የተንጸባረቀውን ይዘት መመርመር፣ 2) በመዝሙሩ የተንጸባረቀውን ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ታሪካዊና ሃይማኖታዊ ዐውዶችን መሠረት በማድረግ መተርጎም፣ 3) ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የፈጸሟቸው ተግባሮች በተፈሪ ማርሽ መንጸባረቃቸውን መመርመርና መተንተን የሚሉት ናቸው፡፡ የተጠቀሱትን ዓላማዎች ለማሳካትም፣ 1) በመዝሙሩ ምን ምን ተንጸባረቀ? 2) መዝሙሩ ያንፀባረቃቸው ይዘቶች ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንን ከፈጸሟቸውና ይፈጽሟቸዋል ከተባሉት ተግባሮች ጋር ምን ያኽል ይጣጣማሉ? 3) ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በዘመናቸው ያከናወኗቸው ተግባሮች በመዝሙሩ ከተንጸባረቁት ይዘቶች ጋር ይጣጣማሉ? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ ተሰጥቷል፡፡ ትንተናው መዝሙሩ የተደረሰበትንና አገልግሎት መስጠት የጀመረበትን ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ታሪካዊ ዐውድ መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያከናወኗቸው ተግባሮችና የተለያዩ ሰዎች ስለ እሳቸው የሰጧቸው አስተያየቶች፣ የምርምር ሥራዎች፣ መጻሕፍትና ጋዜጦች በማገናዘቢየነት አገልግለዋል፡፡

ጥናቱ በቤተ ክህነት ተወስኖ በግእዝ ቋንቋ ብቻ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ይቀርብ የነበረው መዝሙር በሥጋዊ ጉዳይ ላይ ትኩረት በማድረግ በዐማርኛ መቅረብ የጀመረበትን ትክክለኛ ጊዜ ያስዳል፡፡ በውጭ ሀገር የሙዚቃ ትምህርት በተማሩት በኪቮርክ ናልባንዲያን በዘመናዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች የተቀናበረው ተፈሪ ማርሽ የወቅቱን ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ታሪካዊና ሃይማኖታዊ ዕውነታዎች ምን ያኽል እንደተንጸባረቁ ለማወቅ ይረዳል፡፡

በተፈሪ ማርሽ የተንጸባረቀውን ከመመርመራችንና ከመተንተናችን በፊት ስለ መዝሙሩ ስሜነህ (Simeneh, 2006) እና ዮሐንስ (፪ሺ፲) በየጥናታቸው የገለጹትን በአጭሩ እንቃኛለን፡፡ ቅኝታችንንም በስሜነህ ጥናት እንጀምራለን፡፡

በትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር (፲፱፻፳፬) "ተፈሪ ማርሽ"፣ በዮሐንስ (፪ሺ፲) ደግሞ "ማርሽ ተፈሪ" ተብሎ የተጠራው መዝሙር ስሜነህ ከመዘገቡት ሙሉ በሙሉ ይለያል፡፡ እሳቸው "ተፈሪ ማርሽ" ነው ብለው የጠቀሱት "መንግሥትን ለዳዊት" በሚል የሚጠራውን መዝሙር ነው፡፡ ስሜነህ (2006፤ 89) የጠቀሱት መዝሙር ቃል የሚከተለው ነው፡፡

መንግሥትን ለዳዊት ቡራኬን ለሴም፣
እንዳንተ የሰጠው ማንም ሰው የለም፡፡
እንደማቱሳላ እንደ አብርሃም፣
ዕድሜህን ያርዝመው አምላክ ዘለዓለም፡፡
የዘውዱ ምልክት ያገራችን ቤዛ፣
ተነሥታ ብትቆም እሱን ተመርኩዛ፣
ሕዝቡንም ደስ አለው አገኘ ሰላም፣
ከዚህ የበለጠ ምን አለን ዓለም፡፡
የዘውዱ ምልክት ያገራችን ግርማ፣
ክብራችን ጌጣችን ይህ ሰንደቅ ዓላማ፡፡

ስሜነህ ምንጭ ጠቅሰው መዝሙሩ የተደረሰው እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1928 (እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በ1920/1921) ነበር ብለዋል፡፡ ይኸም መዝሙሩ የተደረሰውና አገልግሎት መስጠት የጀመረው በ1917 ዓ. ም. ነው በማለት በዚኽ ጽሑፍ ከተገለጸው ይለያል፡፡ መዝሙሩም ከብሔራዊ መዝሙር እኩል የሚቆጠርና ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዐልጋ ወራሽ በነበሩበት ጊዜ አገልግሎት ይሰጥ እንደ ነበር ያሉት ትክክል ነው፡፡ እሳቸው ተፈሪ ማርሽ ብለው የጠሩት መዝሙር በገሪማ (፲፱፻፺፱፤ 261) እና በተስፋዬ (2005፤ 193) "መንግሥትን ለዳዊት" በሚል ርእስ ተመዝግቧል፡፡ በስሜነህ "ማርሽ ተፈሪ" ተብሎ የተመዘገበውና በተስፋዬ (2005) "መንግሥትን ለዳዊት" በሚል ርእስ የተመዘገበው መዝሙር እኩል ዐሥር ሥንኞች አሉት፡፡ በኹለቱ ሰዎች በተመዘገበው መዝሙር በቃላት አጠቃቀምና በሥንኞቹ አደራደር ቅደም ተከተል ልዩነት ይስተዋላል፡፡ በገሪማ (፲፱፻፺፱) የተመዘገበው መዝሙር በስሜነህ እና በተስፋዬ ከተመዘገበው በሥንኝ ብዛት ልዩነት አለው፡፡ በስሜነህ እና በተስፋዬ በሥንኝነት የተመዘገቡት፡-

የዘውዱ ምልክት ያገራችን ግርማ፣
ክብራችን ጌጣችን ይህ ሰንደቅ ዓላማ፡፡

የሚሉት ሥንኞች በገሪማ በአዝማችነት ተደጋግመው ተመዝግበዋል፡፡ በገሪማ በተመዘገበው መዝሙር መጨረሻው ከተመዘገበው አዝማች በላይ የተመዘገቡት አራት ሥንኞች በስሜነህም፣ በተስፋዬም አልተመዘገቡም፡፡ በስሜነህ እና በተስፋዬ በተመዘገበው መዝሙር የፊደልና የቃላት አጠቃቀም ልዩነት ግን ይስተዋላል፡፡ በገሪማ የተመዘገበው መዝሙር በተስፋዬ ከተመዘገበው

በአዝማችነት በተደጋገሙትና በመጨረሻዎቹ አራት ሥንኞች ከመለያየቱ በስተቀር ሙሉ በሙሉ ይመሳሰላሉ፡፡ በገሪማ የተመዘገበው "መንግሥትን ለዳዊት" የሚለው መዝሙር ዐምስተኛውና ስድስተኛው ሥንኞች በአዝማችነት ሦስት ጊዜ ሲደገሙ በተስፋዬ ግን ይኸ አልተደረገም፡፡ በተስፋዬ በተመዘገበው የሌሉ አራት ሥንኞች በገሪማ ተመዝግበዋል፡፡ ሥንኞቹም ከመጨረሻው አዝማች በላይ የተመዘገቡት ናቸው፡፡ በገሪማ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በወንድና በሴት ፆታ ሲጠራ በተስፋዬ ግን በሴት ፆታ ብቻ ተጠርቷል፡፡ ስሜነህ መዝሙሩን የፍታሔ ንጉሤ መድረሳቸውን እንጂ ተመዝግቦ ያገኙበትን ምንጭ አልገለጹም፡፡ ስለ መዝሙሩ አገልግሎትም አልተናገሩም፡፡ በገሪማ የተመዘገቡትን ተጨማሪ ሥንኞች ሳይጨምር በሦስቱም ሰዎች የተመዘገበው መዝሙር ይዘት ተመሳሳይ ነው፡፡ በገሪማና በተስፋዬ የተመዘገበው መዝሙር በቅደም ተከተል የሚከተለው ነው፡፡

<u>መንግሥት እንደ ዳዊት</u>

መንግሥት እንደ ዳዊት ቡራኬ እንደ ሴም፣
እንዳንተ የተሰጠው አንድም ሰው የለም፡፡
እንደማቱሣላ እንደነ አብርሃም፣
እድሜህን ያርዝመው አምላክ ዘለዓለም፡፡
የዘውዱ ምልክት ያገራችን ግርማ፣
ክብራችን ጌጣችን ይህ ሰንደቅ ዓላማ፡፡
ይህ ሰንደቅ ዓላማ ያገራችን ግርማ፣
ተነሥታ ብትቆም እሱን ተመርኩዛ፣
ሕዝቡንም ደስ አለው አገኘ ሰላም፣
ከዚህ የበለጠ ምን አለን ዓለም፡፡
የዘውዱ ምልክት ያገራችን ግርማ
ክብራችን ጌጣችን ይህ ሰንደቅ ዓላማ፡፡
ሲያወጣ እስራኤልን ከግብፅ አርነት፣
ሦስናንም ሲያድን ከክፉ ጠላት፡፡
የተፈተነ ነው ከአብርሃም ከሙሴ
መድኃኒትነቱ የኃይለ ሥላሴ፡፡
የዘውዱ ምልክት ያገራችን ግርማ፣
ክብራችን ጌጣችን ይህ ሰንደቅ ዓላማ፡፡
(ገሪማ፣ ፲፱፻፷፱፣ 261)

<u>መንግሥት እንደ ዳዊት</u>

መንግሥት እንደ ዳዊት፣ ቡራኬ እንደ ሴም
እንዳንት የተሰጠው፣ አንድም ሰው የለም
እንደ ማቱሳላ፣ እንደነ አብርሃም፣
ዕድሜህን ያርዝመው፣ አምላክ ዘለዓለም!

የዘውዱ ምልክት፣ ያገራችን ግርማ
ክብራችን ጌጣችን፣ ይህች ሰንደቅ ዓላማ
ይህች ሰንደቅ ዓላማ፣ ያገራችን ግርማ
ነሥታ ብትቆም፣ እሱን ተመርኩዛ፣
ሕዝቡንም ደስ አለው፣ አገኘ ሰላም፣
ከዚህ የበለጠ፣ ምን አለን በዓለም!
(ተስፋዬ፣ 2005፣ 193)

ገሪማ የኢጣሊያ ጦር ድል ኾኖ ከኢትዮጵያ በወጣበት በ1933 ዓ. ም. ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ከስደት ተመልሰው ሰንደቅ ዓላማውን ሲሰቅሉ ከሚታየው ፎቶ ግራፍ ሥር መዝሙሩን መመዝገባቸውን እናነባለን፡፡ መዝሙሩን የደረሰውን፣ በዜማ ያቀናበረውንና አገልግሎቱን አልተናገሩም፡፡ እሳቸው በመዘገቡት በዚኸ መዝሙር ከኹለቱም ሰዎች በተለይ የታከሉትን ሥንኞች ምንጭ ማወቅ አልተቻም፡፡ ተስፋዬ (2005) በበኩላቸው ከኢጣሊያ ወረራ በኋላ

በአንደኛና በኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የመዝሙርና የሙዚቃ ክፍለ ጊዚያት ተመድበው ስለ ሀገር ፍቅር፣ ስለ ንጉሠ ነገሥቱና ስለ ሰንደቅ ዓላማ ክብር ይዘመሩ ከነበሩ መዝሙሮች አንዱ መንግሥትን ለዳዊት የሚለው መዝሙር እንደ ነበር ገልጸዋል፡፡ መንግሥትን ለዳዊት ከሚለው መዝሙር በተጨማሪም በተማሪ ቤቶች ይዘመሩ ነበር ያሏቸውን ኹለት ሌሎች መዝሙሮችን መዝግበዋል፡፡ መዝሙሮቹን የደረሳቸውንና በዜማ ያቀናበራቸውን ግን አልገለጹም፡፡ መዝሙቹን አስታውሰው የመዘገቡት በንዋይ ደበበ ተረድተው መመዝገባቸውን በግርጌ ማስታዎሻቸው ገልጸዋል፡፡ ተፈሪ ማርሽ በሚል የሚጠራው መዝሙር በተማሪ ቤቶች ስለመዘመሩ ወይም አለመዘመሩ አላወሱም፡፡ ለማጠቃለል ስሜነህ "ተፈሪ ማርሽ" ብለው የመዘገቡት መዝሙር በገሪማም (፲፱፻፺፱፣ በተስፋዬም (2005) "መንግሥትን ለዳዊት" ተብሎ ከተመዘገበው ጋር ይመሳሰላል፡፡

በትምህርትና ሥነጥበብ ሚኒስቴርም፣ በዮሐንስም የተመዘገበው መዝሙር ከመጠሪያው ጀምሮ መጠነኛ የቃላት አጠቃቀምና የሥንኝ አደራደር ልዩነት ከመስተዋሉ በስተቀር ተመሳሳይ ነው፡፡ በኹለቱ ምንጮች በተመዘገበው መዝሙር የሚስተዋለውን ልዩነትና ተመሳሳይነት ከዚኽ በታች ባለው ንዑስ ርእስ እንመለከታለን፡፡

**2) የ"ተፈሪ ማርሽ" እና የ"ማርሽ ተፈሪ" ልዩነት እና ተመሳሳይነት**

ከዚኽ በላይ የተመለከተው ንዑስ ርእስ በትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር (፲፱፻፷፬፤ 13) "ተፈሪ ማርሽ" በዮሐንስ ደግሞ (፪ሺህ፬፤ 51-52) "ማርሽ ተፈሪ" በሚል መጠራቱን መነሻ ያደረገ ነው፡፡ ኹለቱም ምንጮች መዝሙሩን የጠሩት "ማርሽ" የሚለውን የፈረንሳይኛ ቃል በመጠቀም ነው፡፡ ይኽንን የፈረንሳይኛ ቃል መዝሙሩ ከተደረሰላቸው ሰው ስም ጋር ያዋቀሩት በተለያየ መንገድ ነው፡፡ ትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር የአማርኛውን፣ ዮሐንስ ደግሞ የፈረንሳይኛውን የሰዋስው ሥርዓት መሠረት አድርገው የተዋቀሩትን ጠቅሰዋል፡፡ "ማርሽ"[4] የሚለው የፈረንሳይኛ ቃል የሙዚቃ ዓይነት ኾኖ በጎዳና ወይም በአደባባይ ላይ የሚዘመር ነው፡፡ ከኹለቱ ምንጮች የተገኘውን መዝሙር ልዩነትና ተመሳሳይነት ለመመርመር መዝሙሩን ቀጥለን እንጠቅሳለን፡፡[5]

[4]ውሎ አድሮ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር የተባለው መጀመሪያ "የኢትዮዮጵያ ማርሽ" በሚል ስም ይጠራ ነበር (መርስዔ ኀዘን፣ 1999)፡፡ ይኽም በጊዜው በመዝሙሮቹ አገልግሎትና ባሕርይ ላይ ተመሥርቶ "ማርሽ" የሚለውን ቃል በማከል መጠሪያ የተደረገበት የፈረንሳይኛ ቋንቋ በኢትዮጵያ በነበረው ተፅዕኖ ምክንያት ነው፡፡ በተፅዕኖው ምክንያትም በተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ፈረንሳይኛ ቋንቋን የሚማሩት ተማሪዎች ቁጥር እንግሊዝኛ ቋንቋን ከሚማሩት ይበልጥ ነበር (የተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት አጭር ታሪክ፣ ፲፱፻፺፪)፡፡

[5]የመጀመሪያው ከትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር (፲፱፻፷፬፤ 13)፣ ኹለተኛው ከዮሐንስ (፪ሺህ፬፤ 51-52) የተወሰዱ ናቸው፡፡

<u>ተፈሪ ማርሽ</u>[6]

(1) ኑርልን መሪአችን እንበል አለልን
(2) የኢትዮጵያ ፀሐይ ያፍሪካ ብርሃን
(3) ደማቅ በዓለሙ አብሪ ዙሪያውን
(4) ለሕዝቡም ሙቀቱ ትክክል ሚዛን
(5) መድኃኒት ለድውይ ፋና ለሕጻን
(6) ተፈሪ መኰንን ሽ[ሺ]ሕ ዓመት ኑርልን
(7) አኑረው ኢ.[!]  ፈጣሪ ሕያው አርግልን
(8) ለዘለዓለም ተስፋ መመኪያ እንዲሆን
(9) ለገወኑ [ለወገኑ] ሁሉ ለኢትዮጵያ በድፍን
(10) ተፈሪ መኰንን ካላት ለኛ ሐበሻ
(11) የወራሪው የወራሪው ጠላት የግፍ ምኞት ዋሻ
(12) ተደፍኖ ይቀራል በተፈሪ ጋሻ
(13) ተፈሪ እያለልን አንጠራጠርም
(14) ከነዓን ጥበብን ሳንወርሳት አንቀርም
(15) ለሰ[ስ]ማችን ሞገስ ለደጉ ተፈሪ
(16) ጥበብ ተሰጥቶታል ከላይ ከፈጣሪ

<u>ማርሽ ተፈሪ</u>

ኑርልን መሪአችን
እንበል አለልን
የኢትዮጵያ ፀሐይ የአፍሪካ ብርሃን
ደማቅ በዓለሙ
አብሪ ዝርያውን ለሕዝቡም
ሙቀቱ ትክክል ብርሃን
መድኃኒት ለድውይ
ፋና ለሕጻን
ተፈሪ መኰንን
ሺህ ዓመት ኑርልን
አኑረው ፈጣሪ ሕያው አርግልን
ለዘለዓለም ተስፋ መመኪያ እንዲሆን
ለወገኑ ሁሉ ለኢትዮጵያ በድፍን
ተፈሪ መኰንን ካላት ለኛ ሐበሻ
የወራሪው የወራሪው ጠላት የግፍ ምኞት ዋሻ
ተደፍኖ ይቀራል በተፈሪ ጋሻ
ተፈሪ እያለልን አንጠራጠርም
ከንአን ጥበብን ሳንወርስ አንቀርም
ለስማችን ሞገስ ለደጉ ተፈሪ
ጥበብ ተሰጥቶታል ከላይ ከፈጣሪ።

በትምህርትና ሥነጥበብ ሚኒስቴር የተመዘገበው መዝሙር ደራሲ (የቃሉ) ዮፍታሔ ንጉሤ፣ የዜማው አቀናባሪ ደግሞ ኪቮርክ ናልባንዲያን መኾናቸው ተገልጿል። ዮሐንስ (፻፷ሀ፬፤ 52) በበኩላቸው የመዝሙሩ ደራሲ ዮፍታሔ ንጉሤ አለመኾናቸውን በተዘዋዋሪ መንገድ ገልጸዋል። መዝሙሩም "ከአንድ ሰው ብዕር የፈለቀ አይመስልም። በተለየም የመጨረሻው ስድስት ስንኝና[7] ከእሱ በላይ ያለው።" በማለት በተለያዩ ሰዎች የተደረሰ እንደሚመስላቸው ጠቁመዋል። መዝሙሩን ደርሶታል ብለው የሚገምቱትንም በመጽሐፋቸው ገጽ 51 ላይ "ምናልባት "የኢትዮጵያ ማርሽ"ንና ማርሽ ተፈሪን የደረሰው (ቃሉን) በአንቀጽ 4.4 [ኤፍሬም ተወልደ መድኅን]፣ 4.5 [ኤፍሬም ተወልደ መድኅን] እና 4.6 [መዝሙር ዘመስቀል የሚለውን ልጅ መስፍን ቀለመወርቅ፣ (ኹለቱን ማን እንደደረሳቸው አልገለጹም)] የተጠቀሱትን መዝሙሮች ከደረሷቸው መካከል

[6]በትምህርትና ሥነጥበብ ሚኒስቴር በተመዘገበው መዝሙር ከመዝሙሩ ቃል በፊት የዜማ ምልክቱ ተጽፏል። በዮሐንስ በተመዘገበው መዝሙር የዜማ ምልክቱ አልተመዘገበም።

[7]የዮሐንስ አሰናኝ ስድስቱ ሥንኞች በሌላ ሰው እንደተደረሱ ገምተዋል። ትምህርትና ሥነጥበብ ሚኒስቴር በመዘገበው መዝሙር ከላይ ባሉት ዘጠኝ ሥንኞችና ከታች በተደረደሩት ሰባት ስንኞች መካከል የቦታ ክፍተት እንዲኖር ተደርጓል። ይኽ መኾኑ ግን፣ ከላይ ያሉት ዘጠኝ ሥንኞችና ከታች የተመዘገቡት ሰባት ሥንኞች በተለያዩ ሰዎች የተደረሱ ናቸው የሚል ማስረጃ ነው ብሎ ለመገመት አያስችልም።

አንዱ ወይም አስተሳሰቡ የእነሱን የመሰለ ሌላ ሰው ይሆናል፡፡"በማለት ይገልጻሉ፡፡ በዚኽ አገላለጻቸው የመዝሙሩን ቃል "አልደረሰም" ብለው የሚከራከሩለትን ሰው ማንነት በግልጽ አላስቀመጡም፤ በተዘዋዋሪ መንገድ እንጂ፡፡ ይኸው በመጽሐፋቸው ገጽ 51 ላይ "የኢትዮጵያ ማርሽ" በሚል ርእስ የሚታወቀውን መዝሙር ጠቅሰውና መርስዔ ኀዘንን ዋቢ አድርገው የዮፍታሔ ንጉሤ ድርሰት አይደለም" ብለው እንደሚያምኑ ገልጸዋል፡፡ ከፍ ብሎ በተጠቀሰው ዮሐንስ "የኢትዮጵያ ማርሽንና ማርሽ ተፈን ማን እንደረሳቸው ዐይታወቅም" ማለታቸው ማርሽ ተፈሪ የዮፍታሔ ንጉሤ ድርሰት አይደለም ብለው  እንደሚያምኑ ያስረዳል፡፡ ዮሐንስ "ማርሽ ተፈሪ" የሚለውን መዝሙር ያገኙበት ምንጭ ደራሲውን ስለመግለጹ ወይም ስለ አለመግለጹ ምንም አላሉም፡፡ እንደዚኹም በዜማ ያቀናበረውን አልተናገሩም፡፡ ዮሐንስ "የማርሽ ተፈሪ ደራሲ ዮፍታሔ ንጉሤ አይደለም" የሚል መደምደሚያ ላይ የደረሱት የመዝሙሩ ቃል የተሰናኘበት መንገድ ዜማ የሚሰብርና ዮፍታሔ ከሚታወቅበት የላቀ የግጥም ችሎታ ጋር ስለማይመጣጠን ነው፡፡ ይኹን እንጂ፣ ትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር የግጥሙ ደራሲ "ዮፍታሔ ጉሤ"፣ የዜማው ደግሞ ኪቦርክ ናልባንዲያን ናቸው በማለት ያስረዳል፡፡ ስለኾነም፣  የተለየ ማስረጃ እስከሚቀርብ  ትምህትና ሥነጥበብ ሚኒስቴር የሰጠውን ማስረጃ መቀበል ተገቢ ነው፡፡

ከዚኽ በላይ እንደተመለከተው በትምህርትና ሥነጥበብ ሚኒስቴር እና በዮሐንስ በተመዘገበው መዝሙር መካከል በሥንኝ አደራደርና በጥቂቱም በቃላት አጠቃቀም ልዩነት ይስተዋላል፡፡ በትምህርትና ሥነጥበብ ሚኒስቴር የተመዘገበው መዝሙር በአማርኛ የተለመደውን የሥንኝ አደራደር ሥርዓትን የተከተለና አንድ ሥንኝም በተለያዩ ሐረጎች የሚከፈል መኾኑን በግልጽ ያመለክታል፡፡ በዮሐንስ የተመዘገበው "ማርሽ ተፈሪ"  አብዛኛዎቹ ሐረጎች እንደ ሥንኝ የተደረደሩ ሲኾን፣ ሌሎቹ ደግሞ መደበኛውን የአማርኛ የሥንኝ አደራደር ሥርዓት የተከተሉ ናቸው፡፡ በትምህርትና ሥነጥበብ ሚኒስቴር በተመዘገበው መዝሙር የሥንኝ 1፣ 3፣ 4፣ 5፣ 6 እና 11 ሐረጎች እያንዳንዳቸው በዮሐንስ ሥንኝ ኾነው ተመዝግበዋል፡፡  ከዚኽም በላይ የትምህርትና ሥነጥበብ ሚኒስቴር የአራተኛው ሥንኝ "ለሕዝቡም" የሚለው የመጀመሪያ ሐረግ የመጀመሪያ ቃል በዮሐንስ የሦስተኛው ሥንኝ የኹለተኛው ሐረግ ክፍል ተደርጎ ተመዝግቧል፡፡ ዮሐንስ በመዘገቡት ማርሽ ተፈሪ  የሥንኝ አደራደር ልዩነት የተከሰተው መዝሙሩ ከተቀዳበት ምንጭ ወይም በሌላ ምክንያት ስለመኹኑ አዘጋጁም፣ አሰናኙም አልገለጹም፡፡ ትክክለኛው የተፈሪ ማርሽ የሥንኝ አደራደርም በትምህርትና ሥነጥበብ ሚኒስቴር የተመዘገበው ነው ብሎ መቀበል ግን ተገቢ ነው፡፡

በኹለቱ ምንጮች በተመዘገበው መዝሙር የቃላት አጠቃቀም ልዩነትም ይስተዋላል፡፡ በትምህርትና ሥነጥበብ ሚኒስቴር በተመዘገበው የሦስተኛው ሥንኝ የመጨረሻ ቃል "ዙሪያውን" የሚል ነው፡፡ ዮሐንስ መዝሙሩን ካገኙበት ምንጭ ቃሉ "ዝሪያውን" መባሉንና እሳቸው "ዙሪያውን" በማለት ማስተካከላቸውን ገልጸዋል፡፡ ዮሐንስ የቃሉን የመጀመሪያ ሞኄ እሳቸው ባሉት መልክ ማስተካከላቸው ተገቢም፣ ትክክልም ነው፡፡ በትምህርትና ሥነጥበብ ሚኒስቴር ከተመዘገበው ጋርም በቃሉ አጠቃቀም እንዲጣጣም ኾኗል፡፡ በትምህርትና ሥነጥበብ ሚኒስቴር

በተመዘገበው መዝሙር የአራተኛው ሥንኝ የመጨረሻ ቃል "ሚዛን" የሚል ነው፡፡ ይኸ ቃል በዮሐንስ በተመዘገበው መዝሙር "ብርሃን" በሚል ቃል ተተክቷል፡፡ ቃሉ በስንኙ ከሚገኘው "ሙቀት" ከሚለው ቃል ጋር ተቆራኝቶ ሲነበብ "ብርሃን" የሚለው ቃል ፍቺ ትክክል ይመሳሰላል፡፡ ይኸም ሙቀት ያለው ነገር ብርሃን ይሰጣል ብሎ ከማሰብ የመነጨ ሊኾን ይችላል፡፡ ይኹን እንጂ፣ ወደ ፊት ከምንሰጠው የሐረጉ ትርጉም እንደምንረዳው "ሚዛን" የሚለው ቃል በስንኙ ለመንገር የተፈለገውን ሐሳብ በትክክል ይገልጻል፡፡ "ለሕዝቡም ሙቀቱ" በሚለው በመጀመሪያው ሐረግም፣ "ትክክል ሚዛን" በሚለው በኹለተኛው ሐረግም የተነገሩት ቁም ነገሮች በየራሳቸው ምሉእ ናቸው፡፡ ስለኾነም በትምህርትና ሥነጥበብ ሚኒስቴር የተመዘገበው መዝሙር "ሚዛን" የሚለውን ቃል መጠቀሙ ተገቢ ነው፡፡

በትምህርትና ሥነጥበብ ሚኒስቴር በተመዘገበው ስድስተኛው ሥንኝ የመጀመሪያ ሐረግ "ኢ.[!]"[8] የሚለው ለፈጣሪ ልመና፣ ምልጃ ማቅረቢያ ቃል በዮሐንስ መተመዘገበው መዝሙር ተገድፏል፡፡ "ኢ.[!]" የሚለው ቃል ለእግዚአብሔር የሚቀርበው ተማጽኖ ከፍ ብሎ እንዲሰማ የሚያደርግ ስሜትን ይገልጻል፡፡ ይኸም "ኢ.[!]" የሚለው ቃል ፈጣሪ ለልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንን ሕያው፣ ዘላለማዊ እንዲያደርጋቸው የቀረበው ልመና ጉጉት፣ ከፍተኛ ምኞት በታከለበት ስሜት መቅረቡን ያስረዳል፡፡ በትምህርትና ሥነጥበብ ሚኒስቴር በተመዘገበው መዝሙር ለፈጣሪ የሚቀርበው ተማጽኖ ከፍ ባለ ስሜት በቃል አጋኖ ሲገለጽ በዮሐንስ በተመዘገበው ግን ለፈጣሪ የቀረበው ተማጽዕኖ ዝቅ ወይም ቀዝቀዝ ባለ ስሜት ነው፡፡ ይኸም በኹለቱ ምንጮች በተመዘገበው መዝሙር የተስተዋለው ልዩነት ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ በትምህርትና ሥነጥበብ ሚኒስቴር በተመዘገበው መዝሙር ዘጠነኛውና ዐሥራ ዐምስተኛው ሥንኞች የመጀመሪያዎቹ ሐረጎች የመጀመሪያዎቹ ቃላት ፊደሎች ትርጉም በማይሰጥ እና የተሳሳተ ፍቺ በሚሰጥ መንገድ ተደርድረዋል፡፡ በዮሐንስ በተመዘገበው መዝሙር ግን በትክክል ተደርድረዋል፡፡

በትምህርትና ሥነጥበብ ሚኒስቴር በተመዘገበው መዝሙር "ከነዓን ጥበብን <u>ሳንወርሳት</u> አንቀርም" በሚለው ዐሥራ አራተኛው ሥንኝ የተሠመረበት ቃል በዮሐንስ "ሳንወርስ" በማለት ተመዝግቧል፡፡ ቃሉ በትምህርትና ሥነጥበብ ሚኒስቴር አነስታይ ፆታን እንዲጠራ የተደረገበት ምክንያት "ጥበብ" በአማርኛ በተለምዶ በአነስታይ ፆታ የምትጠራ መኾኑና ቀጥሎ ከሚመጣው ቃል ጋር ተቆራኝቶ ሲነበብ የፆታ ለውጥ እንዲያደርግ ተፅዕኖ በማድረጉ ነው፡፡ ይኹን እንጂ፣ ቃሉ ፆታን ሳይለይ "እኛ" በሚል አንደኛ መደብ ብዙ ቁጥር አመልካች በሚያመለክት ተውላጠ ስም እንዲጠራ ተደርጎ በዮሐንስ "ሳንወርስ" በማለት መመዝገቡ ተገቢ ነው፡፡

---

[8]"ኢ.[!]" በሚለው ቃል አንድ ነጥብ ታክሎበት መቅረቡ ትክክል አይደለም፡፡ ከአንድ ነጥብ ይልቅ የቃል አጋኖ ምልክት መደረጉ ቃሉ የሚኖረው ፍቺ ትክክል ይኾናል፡፡ ቃሉ በጸሎት ሥርዓት ጎላ ብሎና ረዘም ተደርጎ እንደሚሰማው ኹሉ በመዝሙሩም ቃል አጋኖ ምልክት እንዳለው ተደርጎ በተመሳሳይ ለማዜም ያስችላል፡፡

የዮሐንስ (፪ሺ.ህ፬፤ 52) አሰናኘ "...ሌላ የዜማ ጣጣ ከሌለበት በቀር በጥቅሱ ውስጥ እንዳለው መቅረቡ ዜማ ይሰብራል" በማለት ገልጸዋል። ይኸም በመጀመሪያዎቹ ሥንኞች እና ከእነዚኽ በታች በተደረደሩት ስድስት ስንኞች መካከል እንደሚስተዋል አስረድተዋል። "እንዳለ መቅረቡ ዜማ ይሰብራል" ያሏቸው ሥንኞች እሳቸው በመዘገቡት መዝሙር በትክክል የተደረደሩ አይደሉም። ስለኾነም፣ ዜማ መስበሩን ወይም አለመሰበሩን ለመናገር ስንኞቹ በትክክል መደርደራቸው አስፈላጊ ነበር። ስንኞቹ በትክክል ሳይደረደሩ ዜማ ይሰብራል የሚል መደምደሚያ ላይ መድርስ ያስቸግራል።

በትምህርትና ሥነጥበብ ሚኒስቴር የተመዘገበው መዝሙር የመጀመሪያውና ስድስተኛው ሥንኞች "አንተ" በሚል ኹለተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ተባዕታይ ፆታን በሚገልጽ ተውላጠ ስም የተነገሩ ሲኾን ከኹለት እስከ ዐምስት የተደረደሩት ሥንኞች የተነገሩበት አንጻር በግልጽ አልተመለከተም፡ ፡ ይኹን እንጂ፤፤ "አንተ" በሚል አንጻር በተነገሩ ሥንኞች መካከል የተነገሩ በመኾኑ "አንተ" በሚለው አንጻር እንደ ተነገሩ መቁጠር ይቻላል። ከሰባተኛው ሥንኝ ጀምሮ እስከ መጨረሻው የተደረደሩት ሥንኞች "እሱ" በሚል ሦስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ተባዕታይ ፆታ አንጻር የተነገሩ ናቸው። የመጀመሪያዎቹ ስድስት ስንኞች የተነገሩበት "አንተ" የሚለው አንጻር ቀጥለው የተደረደሩት ሥንኞች ከተነገሩበት "እሱ" ከሚለው በተለየ አንጻር መነገራቸው ለዜማው መስበር ምክንያት ኾኖ ይኾን? የሚል ጥያቄ ያስነሣል። ለጥያቄው ትክክለኛውን መልስ ለመስጠት መዝሙሩ ሲዜም ማደመጥ የሚችልበት ዕድል የለም። ከአንድ እስከ ዘጠኝ የተደረደሩት ሥንኞች ቤት የሚመቱት "ን" በሚል ሳድስ ሞኤ ነው። ይኽ መኾኑ የመዝሙሩን ቃል ለሚያነበው ሰው የዜማ መውረድ ያስከትላል። ይኹን እንጂ፣ የመዝሙሩ ቃል የተዘጋጀው ለመነበብ ሳይኾን በዜማ ተቀነብብሮ እንዲደመጥ ነው። የሳድስ ሞኤን በቤት መምቻነት በመጠቀሙ የተፈጠረው ጉድለት በዜማ አቀናባሪው የሚስተካከል በመኾኑ የመዝሙሩ አሠኛኘት ድክመት አለበት ብሎ ለመናገር ያስቸግራል።

ተፈሪ ማርሽ የሚለውን መጠሪያ ከትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር በተጨማሪ ሌሎችም ይጠቀሙበታል። እንደዚኹም "ማርሽ ተፈሪ" የሚለውን መጠሪያ ከዮሐንስ በፊትም፣ በኋላም ሌሎች በርካታ ሰዎች መዝሙሩን ጠርተውበታል። ይኽንንም ወደፊት የተለያዩ ምንጮችን በመጥቀስ በምናደርገው ምርመራ እንመለከታለን። በዚኽ ጥናት ትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር መዝሙሩን የጠራበትን ተፈሪ ማርሽን ተጠቅመናል። ይኽ የተደረገው ጥናቱ በምንጭነት በተጠቀመበት በትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር የተመዘገበው መዝሙር ተፈሪ ማርሽ የሚለውን መጠሪያ መጠቀሙ ነው። የዚኽ መዝሙር አገልግሎት ምን እንደ ነበረ ለመረዳት ይዘመርባቸው የነበሩትን አጋጣሚዎች ቀጥሎ በተመለከተው ንዑስ ርእስ እንመለከታለን።

## 3) ተፈሪ ማርሽ የተዘመረባቸው አጋጣሚዎች

በዚኽ ንዑስ ርእስ ተፈሪ ማርሽ መቼ? የት? እንዴት? አገልግሎት ይሰጥ እንደ ነበር በ"ብርሃንና ሰላም" ጋዜጣ የተዘገበውንና በጥቂት መጻሕፍት የተገለጸውን መሠረት በማድረግ ለመረዳት ጥረት ተደርጓል። ከእነዚኽ ምንጮች የተገኘው መረጃ ተፈሪ ማርሽ የተዘመረባቸውን ኹሉንም አጋጣሚዎች ሊነግር አይችልም። ይኹን እንጂ፣ ተጨማሪ መረጃ ለመሰብሰብና ለመመርመር ጊዜም፣ የሚገመቱ መረጃዎች ተሟልተው አለመገኘትም በተጠቀሱት መረጃዎች መወሰን ግድ ኾኗል። ይኽም ኾኖ፣ ከተጠቀሱት የመረጃ ምንጮች የተገኘው መረጃ ተፈሪ ማርሽ የተዘመረባቸውን አጋጣሚዎች ለመገንዘብ በማሳያነት አገልግሏል። ቀጥሎም መዝሙሩ የተዘመረባቸው የተወሰኑ አጋጣሚዎች ይቀርባሉ።

ተፈሪ ማርሽ ለመጀመሪያ ጊዜ የተዘመረው የተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት በተከፈተበት ሚያዝያ 19 ቀን 1917 ዓ. ም. ነው። ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በመሳፍንቱና በመኳንንቱ እንዲኹም በሌሎች ተጋባዦች ታጅበው ትምህርት ቤቱ ሲደርሱ "የአርመን ልጆች "ማርሽ ተፈሪ" የሚባለውን አዲሱን መዝሙር ዘመሩ (መርስዔ ኀዘን፣ 1999፤ 279)። እንዲሁም ተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት የተመሠረተበት ዓመታዊ መታሰቢያ በዐል ሚያዝያ 29 ቀን 1918 ዓ. ም. በሙሴ [monsieur] ግሌዝ ሆቴል ሲከበር በዓሉን ለማክበር ተጋባዥ እንግዶች በተሰበሰቡበት ቦታ ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ሲደርሱ ሙዚቀኞች ማርሽ ተፈሪን እየዘመሩ ተቀብለዋቸዋል[9]

በ1919 ዓ. ም. የመስቀል ደመራ በዐል በፍል ውሃ ሜዳ ሲከበር ሙዚቀኞች "የኢትዮጵያ ማርሽ"ን[10] እና የ"ተፈሪ ማርሽ"ን እንዲኹም ልዩ ልዩ ማርሽም ያዜሙ ነበር።[11] "ልዩ ልዩ ማርሽ" የተባሉትን የመዝሙር ዓይነቶችና አገልግሎታቸውን ለመረዳት አልተቻለም። የመዝሙሮቹ ቃልም በ"ብርሃንና ሰላም" ጋዜጣ ተመዝግቦ አልተገኘም።

ሐምሌ 30 ቀን 1920 ዓ. ም. ለዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሽልማት በሚሰጥበት ሥርዓት ላይ ለመታደም ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ወደ ትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ሲገቡ ተማሪዎቹ ተሰልፈው "የኢትዮጵያን ማርሽ እየሙቱ" ተቀበሏቸው። ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንና የተጋበዙ እንግዶች ወደ አዳራሹ ከገቡ በኋላ "ማርሽ ተፈሪ" ተዘመረ። ከዚኽ በኋላ መጀመሪያ ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ያገር ግዛት ሚኒስቴር በአማርኛ፣ ቀጥሎም ሙሴ [monsieur] ዋዲዕ ዜከ በፈረንሳይኛ ንግግር አድርገው እንዳበቁ ተማሪዎቹ "የኢትዮጵያን ማርሽ" ዘመሩ። መዝሙሩ ከተዘመረ በኋላ፣ በትምህርታቸው የተሻለ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች ሽልማታቸውን ከልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን እጅ ተቀበሉ። ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ

---

[9] ብርሃንና ሰላም፣ ኹለተኛ ዓመት፣ ቁጥር ፲፱፣ ኀሙስ ግንቦት ፫ ቀን ፲፱፻፲፰።

[10]"የኢትዮጵያ ማርሽ" ተብሎ የተጠራው ከጊዜ በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር የተባለው ነው። "የኢትዮጵያ ማርሽ" ለመጀመሪያ ጊዜ ተዘመረ የተባለው በ1919 ዓ. ም. ነው (መርስዔ ኀዘን፣ 1999)። ይኽም "ተፈሪ ማርሽ" አገልግሎት መስጠት ከጀመረ ቢያንስ አንድ ዓመት ተኩል ዘግይቶ ማለት ነው።

[11] ብርሃንና ሰላም፣ ኹለተኛ ዓመት፣ ቁጥር ፴፱፣ ኀሙስ መስከረም ፳ ቀን ፲፱፻፲፱፣ ፫፻፯።

መኰንን የማሳረጊያውን ንግግር ካደረጉ በኋላ፣ "ሙዚቃ እየተመታና በሙዚቃ እየተመሩ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ የሚመስል ልብስ የለበሱ ሕፃናት የጅምናስቲክ ሰልፍ"[12] አሳይተው የዕለቱ ዝግጅት ተጠናቀቀ፡፡ የዕለቱ ዝግጅት ታዳሚዎችን "የኢትዮጵያ ማርሽ" (የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር) ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንን ለመቀበል ደግሞ "ማርሽ ተፈሪ" ተዘምረዋል፡፡ ይኸም፣ በኹለቱ ትምህርት ቤቶች ሐምሌ 30 ቀን 1920 በተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ለነበረው ዝግጅት ማዝጊያ ኾኖ የተዘመረው "የኢትዮጵያ ማርሽ" ነው፡፡

መስከረም 27 ቀን 1921 ዓ. ም. ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን "ንጉሥ ተብለው የኢትዮጵያ መንግሥት ዐልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ" የኾኑበት በ"ብርሃንና ሰላም"[13] ጋዜጣ እንደተዘገበው ከቤተ መንግሥቱ በስተ ምሥራቅ በኩል ባለው በር የንግሥና ሥርዓቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ወደ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ቤት በሰልፍ ጉዞ ይደረጋል፡፡[14] ከሰልፎቹ የመጨረሻው ረድፍ ላይ የሚገኙት የተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት ተማሪዎች "ተፈሪ ማርሽ"ን ይዘምሩ ነበር፡፡ በእንዲኽ ዓይነቱ ብሔራዊ ሥርዓተ ክዋኔ ላይ "ተፈሪ ማርሽ" እንዲዘመር ማድረግ በንጉሡም፣ በሥርዓተ ንግሡ መርሐ ግብር መሪ/ዎችም ለመዝሙሩ የተሰጠው ቦታ ከፍተኛ እንደ ነበር ይጠቁማል፡፡ በሌላ በኩል፣ በዕለቱ "የኢትዮጵያ ማርሽ" አለመዘመሩ ስለ ብሔራዊ መዝሙር አገልግሎት የነበረው ግንዛቤ ዝቅተኛ እንደ ነበር ያስረዳል፡፡

ኅዳር 24 ቀን 1922 ዓ. ም. የፍራንኮ ኢትዮጵያ ኩባንያ ፕሬዚዳንት ከፈረንሳይ፣ የጂቡቲ ሀገረ ገዢ፣ የባሕር ኃይል አለቆችና ወታደሮች የባቡር ማረፊያ ቤት ምረቃ በዓል ለማክበር ወደ አዲስ አበባ መጡ፡፡ የባቡር ማረፊያ ቤቱን ለመመረቅ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን በከቡራን መኳንንቶቻቸው ታጅበው በቦታው ሲደርሱ ተሰልፎ ይጠባበቅ የነበረው የከተማው ዘበኛ ሰላምታ ሰጠ፡፡ ቀጥሎም የፈረንሳይ የባሕር ኃይል ወታደሮች በሙዚቃ ሰላምታ ሰጥተው ማርሽ ኢትዮጵያን ነፉ፡፡ ከዚኽ በኋላ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥ የተሠራውን ቤት ክፍሎች ተመልከተው ለግርማዊ ንጉሥ ዳግማዊ ምኒልክ፣ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት፣ ለልዑል ራስ መኰንንና ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ከነሐስ ከተሠራው ሐውልቱ ፊት ለፊት በተዘጋጀላቸው ቦታ ላይ ተቀመጡ፡፡[15] ስለ ተሠራው ቤት፣ ስለ ባቡር አገልግሎትና ስለ ኢትዮጵያና ፈረንሳይ መንግሥታት የተለያዩ ሰዎች ንግግር አድርገው እንደ ጨረሱ ግብዣ መደረጉ በጋዜጣው ተዘግቧል፡፡ የፈረንሳይ ባሕር ኃይል ወታደሮች "በሙዚቃ ሰላምታ ሰጡ" የሚለው የፈረንሳይ ብሔራዊ መዝሙር መዘመራቸውን ይኾን? መልሱ አዎን

---

[12] <u>ብርሃንና ሰላም</u>፣ አራተኛ ዓመት፣ ቁጥር ፳፰፣ ኀሙስ ነሐሴ ፫ ቀን ፲፱፻፳፡፡

[13] <u>ብርሃንና ሰላም</u>፣ አራተኛ ዓመት፣ ቁጥር ፴፩፣ ኀሙስ ጥቅምት ፩ ቀን ፲፱፻፳፩

[14] ወደ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ቤት በሰልፍ በተደረገው ጉዞ፣ "መጀመሪያ መለከተኞች እየነፉ አለፉ፡፡ ቀጥሎ ከየደንቡ የተመረጡ የሻምበሎች ጎፈር ለብሰው በፈረስ እያናጠሩ አለፉ፡፡ ቀጥሎ ነጋሪት መቺዎች በበቅሎ ሆነው እየጎሰሙ አለፉ፡፡ ቀጥሎ እምቢልተኞችና ጥሩንባ ነፊዎች በየስልቱ እየነፉ አለፉ፡፡ ቀጥሎ መትረየስ አንጋች ፈረሰኞች በሚያስደንቅ ሰልፍ አለፉ፡፡ ቀጥሎ የንጉሡ ፋንፋር ሙዚቃ እየመቱ አለፉ፡፡ ቀጥሎ የክብር ዘበኞችና ሰማያዊ ኮት የለበሱ ፈረሰኞች አለፉ፡፡ <u>ቀጥሎ የተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተፈሪ መኰንንን ማርሽ እየመቱ አለፉ</u>፡፡ ቀጥሎ ሰይፈ ጃግሬዎች ሰይፋቸውን እየመዘዙ ይዘው ከንጉሡ ሰረገላ ግራና ቀኝ ሆነው በግርማ እየታዩ አለፉ፡፡" (አጽንኦት የታከለ) (<u>ብርሃንና ሰላም</u>፣ አራተኛ ዓመት፣ ቁጥር ፴፩፣ ኀሙስ ጥቅምት ፩ ቀን ፲፱፻፳፩፣ ፫፻፳፬)፡፡

[15] ብርሃንና ሰላም፣ ዐምስተኛ ዓመት፣ ቁጥር ፴፱፣ ኀሙስ ኅዳር ፳፮ ቀን ፲፱፻፳፪፡፡

ከኾነ ቀድሞ የእንግዳው ሀገር፣ ቀጥሎ የኢትዮጵያው "ማርሽ ኢትዮጵያ" (በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር) መዘመሩ በዐኹኑ ዘመን ከሚከወነው የእንግዳ አቀባበል ሥርዓት ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

ሰኔ 28 ቀን 1922 ዓ. ም. የተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት በዓመቱ መጨረሻ የተሻለ ውጤት ያመጡ የተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት ተማሪዎችን ለመሸለም የተዘጋጀውን በዓል ለማክበር ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ ብፁዓን ጳጳሳትና ሌሎችም ታላላቅ መኳንንት፣ ወይዛዝርና የውጭ ሀገር ሰዎች በቦታው ሲደርሱ ተማሪዎች ልብ የሚሰርቅ ሙዚቃ እየነፉ ተቀበሏቸው፡፡ ከተማሪዎቹ ሙዚቃ ቀጥሎ "ሲግናሊስት" "የኢትዮጵያን መዝሙር በሚአምር ሙዚቃ ዘመሩ፡፡" እንግዶቹ ለበዓሉ በተዘጋጀው አዳራሽ ከገቡ በኋላ ተማሪዎቹ በፈረንሳይኛ፣ በእንግሊዝኛ፣ በግእዝና በዐማርኛ መዝሙሮችን ዘምረዋል፡፡ በዐማርኛ፣ "የኢትዮጵያ መዝሙር" በሚል ርእስ፣ በግእዝ ደግሞ "መዝሙር" በሚል ርእስ  የቀረቡ ናቸው፡፡ በዐማርኛና በግእዝ ቋንቋዎች የተዘመሩት መዝሙሮች በጋዜጣው ላይ ተጽፈዋል፡፡ በዕለቱ  መርሐ ግብር መጨረሻ ላይ ቀድሞ "የፈረንሳዊ ማርሽ ሙዚቃ"፣ ቀጥሎ ደግሞ "ተፈሪ ማርሽ" ተዘመሩ፡፡ "ተፈሪ ማርሽ" ሲዘመር፣ ጃንሆይ፣ መኳንንቱና የውጭ አገር ሰዎች ኹሉም ተነሥተው ቆሙ፡፡ መዝሙሩ ተዘምሮ እንዳበቃ የዕለቱ መርሐ ግብር ተጠናቀቀ፡፡ ከዚኽ በኋላ የውጭ አገር ሰዎች እየተሰናበቱ ኼዱ፡፡[16] በመርሐ ግብሩ መጨረሻ "ተፈሪ ማርሽ" መዘመሩና ጃንሆይም፣ በዝግጅቱ የታደሙት መኳንንትና የውጭ ሀገር ሰዎችም ከተቀመጡበት መነሣታቸው በጊዜው የብሔራዊ መዝሙር ሚና እንደ ነበረው ያስረዳል፡፡

የካቲት 20 ቀን 1923 ዓ. ም. ግርማዊት እቴጌ መነን ከማታው ኹለት ሰዓት ስድስተኛ ወንድ ልጅ ወለዱ፡፡ በማግሥቱ የካቲት 21 ቀን ጃንሆይ በማለዳ ወደ እንጦጦ ማርያም ወጥተው ግርማዊት እቴጌ በደኅና ስለመገላገላቸውና ወንድ መስፍን ስለመውለዳቸው ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀረቡ፡፡ ጃንሆይ ወደ ቤተመንግሥታቸው ተመልሰውም በዙፋናቸው ላይ ተቀምጠው ደስታቸውን ለመካፈል የመጡ እንግዶች በየተራ እየገቡ "እንኳን ደስ አለዎ" እያሉ መልካም ምኞታቸውን እየገልጹ እንዲመለሱ ፈቅደው አስተናገዱ፡፡ አራት ሰዓት ሲኾነ ወታደሮች በግቢው ውሥጥ ተሰልፈው የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙርንና "ማርሽ ተፈሪ"ን እየዘመሩ ደስታቸውን ገለጡ፡፡[17]

ሰኔ 27 ቀን 1923 ዓ. ም. ከተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ተማሪዎች የላቀ ውጤት ያመጡትን ለመሸለም በዳግማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤት ባለው አዳራሽ ዝግጅት ተደረገ፡፡ ተማሪዎቹ ሽልማታቸውን በሚቀበሉበት ዕለት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ የሃይማኖት አባቶች፣ የሀገር ውስጥ ሰዎችና የአውሮፓ መንግሥታት መልእክተኞች በእንግድነት ተገኙ፡፡ በዝግጅቱ መጀመሪያ "የፓሪስ ፀደይ" ቀጥሎ "የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር" (የኢትዮጵያ ማርሽ ይባል የነበረው) ተዘመሩ፡፡ በዝግጅቱ ማጠናቀቂያ ላይ "ማርሽ ተፈሪ" ሲዘመር ኹሉም እንግዶች

[16] ብርሃንና ሰላም፣ ስድስተኛ ዓመት፣ ቁጥር ፳፰፣ ኀሙስ ሐምሌ ፫ ቀን ፲፱፻፳፪፡፡
[17] ብርሃንና ሰላም፣ ሰባተኛ ዓመት፣ ቁጥር ፲፣ ኀሙስ የካቲት ፳፮ ቀን ፲፱፻፳፫፡፡

ከተቀመጡበት ተነሥተው ቆሙ፡፡ መዝሙሩ ተዘምሮ ካበቃ በኋላ የዕለቱ መርሐ ግብር ተጠናቀቀ፡፡[18]

በዝግጅቱ ላይ ከተዘመሩት ሦስት መዝሙሮች "የፓሪስ ፀደይ" የሚለውን መዝሙር ቃል ለማግኘት አልተቻለም፡፡ በዝግጅቱ መጀመሪያ ላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር፣ በዝግጅቱ ማጠቃለያ ላይ ደግሞ ማርሽ ተፈሪ መዘመራቸው በአንድ በኩል የአገልግሎት መመሳሰል መኖሩን ይነግራል፡፡ በሌላ በኩል በዝግጅቱ ማጠቃለያ ላይ ማርሽ ተፈሪ መዘመሩና የዝግጅቱ ታዳሚዎች ከተቀመጡበት መነሣታቸው ከኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር የበለጠ ቦታ እንደተሰጠው ያስረዳል።

ሐምሌ 4 ቀን 1923 ዓ. ም. የዳግማዊ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሽልማት የሚሰጥበትን ቀን ለማክበርና ሽልማት ለመስጠት ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ ብፁዓን ጳጳሳትና ልዑላን መሳፍንት፣ ክቡራን መኳንንትና ሊቃውንት፣ የአውሮፓ መንግሥታት መልእክተኞች፣ ሚኒስትሮችና ቆንስሎች፣ የዲፕሎማቲክ ሰዎች ሥርዓቱ በሚከወንበት አዳራሽ ተገኙ፡፡ በመጀመሪያ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር ተዘመረ፡፡ ከዚኽ ቀጥሎ ቲያትር ቀርቧል፤ "የሰልፍ መዝሙር"ና የፈረንሳይ መዝሙር ተዘምረዋል፡፡ በዝግጅቱ ፍጻሜም "የተፈሪ መዝሙር በሙዚቃ ተዘመረ፡፡"[19] በማለት ተዘግቧል፡፡ "የተፈሪ መዝሙር" የሚለው ተፈሪ ማርሽን ነው፡፡

ሐምሌ 16 ቀን 1923 ዓ. ም. የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የልደት ቀን በታላቁ ቤተ መንግሥት ሲከበር "የመጀመሪያው የኢትዮጵያ መዝሙር በሙዚቃ ተዘመረ፡፡" ከዚኽ መዝሙር በኋላ በፈረንሳይኛ ቋንቋ የተዘጋጀ ቲያትርና ሌሎች የተለያዩ መዝሙሮች ተዘምረዋል፡፡[20] በዚኽ የልደት ቀናቸው ላይ ተፈሪ ማርሽ መዘመሩ አልተዘገበም፡፡ የኢትዮጵያ መዝሙር እንደ ተዘመረ የተዘገበውም የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር ስለመኾኑ እርግጠኛ መኾን አይቻልም፡፡ በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ዳይሬክተር በነበሩት በበቀለ የተደረሰውና በትምህርት ቤቱ ይዘመር የነበረው መዝሙር የኢትዮጵያ መዝሙር ተብሎ መጠራቱ የኢትዮጵያን ጉዳይ የሚያነሳ መዝሙር ኹሉ የኢትዮጵያ መዝሙር እየተባለ ይጠራ ነበርና፡፡

በነሐሴ 16 ቀን 1923 ዓ. ም. ከፈረንሳይ ሀገር "የመጀመሪያው የአየር ባቡር" [አውሮፕላን] ወደ ዐዲስ አበባ መምጣቱን ምክንያት በማድረግ በተደረገው የአቀባበል ሥርዓት ላይ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ንግግር ያደርጋሉ፡፡ ከእሳቸው ንግግር በኋላ መጀመሪያ "ማርሽ ተፈሪ" ቀጥሎ ማርሼዝዬ" ["ላ ማርሰዬዝ"፣ La Marseillaise] [የፈረንሳይ ብሔራዊ መዝሙር] ተዘመሩ፡፡[21] በዚኽ ሥርዓት ላይ "ማርሽ ተፈሪ" የብሔራዊ መዝሙር ሚና እንዲኖረው ተደርጓል፡፡ በጋዜጣው

---

[18] <u>ብርሃንና ሰላም</u>፣ ሰባተኛ ዓመት፣ ቁጥር ፳፰፣ ኀሙስ ሐምሌ ፬ ቀን ፲፱፻፳፫፡፡
[19] <u>ብርሃንና ሰላም</u>፣ ሰባተኛ ዓመት፣ ቁጥር ፴፣ ኀሙስ ሐምሌ ፲፮፲፱፻፳፫፡፡
[20] <u>ብርሃንና ሰላም</u>፣ ሰባተኛ ዓመት፣ ቁጥር ፴፣ ኀሙስ ሐምሌ ፲፮፲፱፻፳፫፡፡
[21]"በኢትዮጵያ መጀመሪያ የአየር ባቡር ስለ መምጣትና አዲስ አበባ ስለ መግባት"፤ <u>ብርሃንና ሰላም</u>፣ ዐምስተኛ ዓመት፣ ቁጥር ፴፬፣ ኀሙስ ነሐሴ ፲፮ ቀን ፲፱፻፳፩፤ ፪፻፸፫፡፡

ዘገባ መሠረት የእንግዳው ሀገር ብሔራዊ መዝሙር ከ"ማርሼዝዬ" ቀድሞ የተዘመረው "ማርሽ ተፈሪ" ነው፡፡[22]

በሐምሌ 14 ቀን 1924 ዓ. ም. የቅዱስ ጊዮርጊስ ተማሪ ቤት ለዕረፍት በሚዘጋበት ቀን በተደረገው ዝግጅት የኢትዮጵያ መንግሥት ዐልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን፣ ልዑል ራስ ሥዩም ሌሎችም የኢትዮጵያ ሕዝብ መኳንንትና የውጪ ሀገር ሰዎች ተጋብዘው ነበር፡፡ ተጋባዥ እንግዶች በዝግጅቱ ላይ እንደ ታደሙ "የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር" ተዘመረ፡፡[23] ከዚኽ በኋላ የትምህርትና የጥበብ ሚኒስትር መልአከ ሕይወት ወልደ ሐና ንግግር አርገዋል፡፡

የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትምህርት ቤት የክረምቱን እረፍት ምክንያት በማድረግ ሐምሌ 21 ቀን 1924 ዓ. ም. በሚዘጋበት ዕለት በትምህርታቸው የበለጠ ውጤት ላገኙ ተማሪዎች ሽልማት ለመስጠት ዝግጅት ይደረጋል፡፡ በዝግጅቱ ላይም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ ግርማዊት እቴጌ መነን፣ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት ዐልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን፣ ልዑላን መሳፍንት፣ ከቡራን መኳንንት፣ ሚኒስትሮች ልዑላት ወይዛዝርና የውጪ ሀገር የኮር ዲፕሎማቲክ ሰዎች በቦታው ሲደርሱ "የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር" ተዘመረ፡፡[24] ንጉሠ ነገሥቱ በሚገኙበት ዝግጅት ላይ "ተፈሪ ማርሽ" መዘመሩ አልተዘገበም፡፡ የዚኽ ምክንያት፣ አንድም የጋዜጣው ዘጋቢ ትኩረት የሰጠው ለኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር በመኾኑ ነው፡፡ አንድም፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር የማርሽ ተፈሪ አገልግሎት በመተካቱ ነው፡፡

ሐምሌ 16 ቀን 1924 ዓ. ም. የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የልደት ቀን ሲከበር ከንጋቱ 12 ሰዓት ክብር 23 ጊዜ መድፍ ተተኰሰ፡፡ ከጧቱ አንድ ሰዓት ጀምሮ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የክብር ዘበኞች በአለቃ በአለቃቸው ከ4 ኪሎ ጀምረው እስከ ቤተመንግሥቱ ደረጃ ድረስ በመንገዱ ግራና ቀኝ ተሰልፈው ለሰው ኹሉ ሰላምታ እየሰጡ ያልፉ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ መኳንንትና የውጪ ሀገር ሰዎች ወደ ቤተ መንግሥቱ ገብተው በየማዕረጋቸው ከተቀመጡ በኋላ በሻምፓኝ ግብዣ ጊዜ የሚኒስትሮች [አምባሳደሮች] ተወካይ ንግግር አደረጉ፡፡ ቀጥሎም "የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር በሙዚቃ ድምጽ ተዘመረ፡፡" መዝሙሩ ከተዘመረ በኋላ የውጪ ሀገር ሚኒስትሮችና ቆንስሎች ጃንሆይን እየተሰናበቱ ኼዱ፡፡ የመንግሥት ሠራተኞች፣ የከተማ ኑዋሪዎች፣ የውጪ ሀገር ሰዎች፣ የኢትዮጵያ ዐርበኞችና የየክፍሉ ሹማምንት "እንኳን ከዚኽ አደረሰዎ፤ ደግሞ ብዙ ዘመን ያኑርዎ" እያሉ እጅ እየነሱ ወጡ፡፡[25] በመርሐ ግብሩ ማጠናቀቂያ ላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር ተዘምሯል፡፡ በዚኽ ዝግጅት ላይ ተፈሪ ማርሽ መዘመሩ አልተዘገበም፡፡

---

[22]ይኽም በዐኹኑ ጊዜ የእንግዳውን ሀገር ብሔራዊ መዝሙር በማስቀደም ከሚዘመረው ልምድ ጋር የተጣጣመ አይደለም፡፡

[23] <u>ብረሃንና ሰላም</u>፣ ስምንተኛ ዓመት፣ ቁጥር ፴፮፣ ኀሙስ ሐምሌ ፳፩ ቀን ፲፱፻፳፬፤ ፪፻፵፫፡፡

[24]<u>ብርሃንና ሰላም</u>፣ ስምንተኛ ዓመት፣ ቁትር ፴፫፣ ኀሙስ ነሐሴ ፫ ቀን ፲፱፻፳፬፤ ፪፻፶፯ ፡፡

[25] <u>ብረሃንና ሰላም</u> ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፴፮ ኀሙስ ሐምሌ ፳፩ ቀን ፲፱፻፱፬፤ ፪፻፵፡፡

ሐምሌ 16 ቀን 1925 ዓ. ም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የልደት ቀን በቤተ መንግሥት ሲከበር የውጭ ሀገር ሚኒስትሮችና ቆንስሎች በየማዕረጋቸው ወደ ጃንሆይ እየቀረቡ ሰላምታ ሲሰጡ "ማርሽ ተፈሪ" ተዘመረ፡፡ በዝግጅቱ ላይ የውጭ ሀገር ሚኒስትሮች ተወካይ ስለ ጃንሆይ የልደት በዓል ንግግር አደረጉ፡፡ በመርሐ ግብሩ መዝጊያ ላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር ተዘምሮ የውጭ ሀገር ሚኒስትሮችና ቆንስሎች ጃንሆይን እየተሰናበቱ ኼዱ፡፡[26] እንግዶችን ለመቀበል ወይም መርሐ ግብሩ መጀመሩን ለማብሰር "ማርሽ ተፈሪ" መዘመሩን ኹለቱም መዝሙሮች በአንድ አጋጣሚ ላይ የሚዘመሩበትን ቅደም ተከተል ያስረዳል፡፡ ይኽ ቅደም ተከተል ግን ሌላ ጊዜ ወጥ በኾነ መንገድ እንደማይተገበር መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡

ከኢጣልያ ወረራ በኋላ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የ12ኛው ዓመት የዘውድ በዓልና የአማካሪ ምክር ቤትን ለመክፈት በተዘጋጀው በዓል "ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ከመሳፍንቶቻቸውና ከመኳንቶቻቸው ጋር በደረሱ ጊዜ በክብር ዘበኛ ሙዚቀኛ "ማርሽ ተፈሪ" ተመታ፡፡" ግርማዊ ነጉሠ ነገሥት ምክር ቤቱን ለመክፈት የተዘጋጀውን ዲስኩር ተናግረው እንደ አበቁ የዕለቱ መርሐ ግብር ተፈጸመ፡፡[27] በእንዲኽ ዓይነቱ ሀገራዊ ዝግጅት ላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር መዘመሩ አልተዘገበም፡፡ ያለመዘገቡ ምክንያት አንድም፣ በጊዜው የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር ባለመዘመሩ ነው፡፡ አንድም፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር ለመዘመሩ የጋዜጣው ዘጋቢ ትኩረት ባለመስጠቱ ነው፡፡

ሚያዝያ 27 ቀን 1936 ዓ. ም. አደባባይ ሐውልት በተመረቀበት ዕለት ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በሐውልቱ መግቢያ በር ላይ የተታታውን ክር በወርቅ መቀስ ቆርጠው ወደ ውስጥ በመግባት ሐውልቱ የተሸፈነበትን ሰንደቅ ዓላማ እንዲነሣ አድርገው ወደ ቦታቸው ተመልሰው እንደቆሙ "የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር" ተዘመረ፡፡ በዕለቱ ዝግጅት ላይ "ተፈሪ ማርሽ" መዘመሩ በዐማርኛ አልተዘገበም፡፡ ነገር ግን፣ የዕለቱ ዝግጅት ተጠናቅቆ ግርማዊ ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ወደ ቤተ መንግሥታቸው ሲኼዱ "ተፈሪ ማርሽ" መዘመሩ በዐማርኛ ከተዘገበው ጎን በእንግሊዝኛ ተዘግቧል፡፡ በእንግሊዝኛ የተዘገበውም የሚከተለው ነው፡፡

> The Monument was unveiled in the presence of Dignitaries and Ministers, the Diplomatic Corps and leading foreign personalities.The Band of the Imperial Guard then played the Ethiopian National Hymen. As His Imperial Majesty departed for the Palace, the <u>Tafari March</u> was played, and school children who had assembled with flags and banners appropriate song for the occasion[28] (emphasis is mine).

[26]<u>ብርሃንና ሰላም</u>፣ ዘጠነኛ ዓመት፣ ቁጥር ፳፱ ፣ ኀሙስ ሐምሌ ፯ ቀን ፲፱፻፳፭፡፡
[27]የጽሕፈት ሚኒስቴር የጋዜጣና የማስታወቂያ ጽሕፈት ቤት ተጻፈ፤ "ስለ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ያ፲፪ተኛው ዓመት የዘውድ በዓል በተለይ የወጣ"፤ <u>ብርሃንና ሰላም</u>፣ ጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፱፻፴፫፡፡
[28] <u>ብርሃንና ሰላም</u>፣ ጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፱፻፴፮፡፡

ከዚኽ በላይ በተጠቀሰው የእንግሊዝኛ ዘገባ መሠረት ተፈሪ ማርሽ በሐውልቱ ምረቃ ሥነሥርዓት መጀመሪያ ላይ ወይም በሐውልቱ ምረቃ ፍጻሜ ላይ አልተዘመረም፡፡ ተፈሪ ማርሽ የተዘመረው ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሐውልቱን መርቀው ወደ ቤተ መንግሥታቸው ሲኼዱ ነው፡፡ ይኸም በሌላ ጊዜ ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን/ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በዝግጅቱ ቦታ ሲደርሱ ወይም የዝግጅቱ መርሐ ግብር ሲጠናቀቅ ከሚዘመረው ይለያል፡፡

የኢጣልያ ቅኝ ገዢ ጦርን በጦር መሣሪያ ለታገሉ ዐርበኞችና "ለጠላት አንገዛም" በማለት ንብረታቸውን ጥለው ለተሰደዱ፤ በውስጥ ኾነው እርዳታ ላደረጉ የውስጥ ዐርበኞችና ለሰንደቅ ዓላማው የክብር ሽልማት ለመስጠት ጥር 12 ቀን 1937 ዓ. ም. በጃንሆይ ሜዳ በተዘጋጀው በዓል ላይ ማርሽ ተፈሪ እና "የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር" ተዘምረዋል፡፡ ማርሽ ተፈሪ የተዘመረው "ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ልዑል ዐልጋ ወራሽንና ልዑል መኰንንን አስከትለው፣ በመሳፍንቱና በመኳንንቱ ታጅበው ከጧቱ በ፩ ሰዓት በጃንሆይ ሜዳ" ደርሰው በሰልፉ መሀል አልፈው ወደ ዙፋናቸው ይሚኼዱ በነበረበት ጊዜ ነው፡፡ በዕለቱ ጠላትን በመሣሪያ ለተከላከሉና ካገር እንዲወጣ ለማድረግ ለሠሩ፣ በጦርነቱ ላይ ለወደቁ ኢትዮጵያውያን ለውለታቸው ንጉሠ ነገሥቱ ሽልማት ሰጡ፡፡ በዕለቱ ሽልማት የመስጠት ሥርዓት ከተፈጸመ በኋላ የጦር ሠራዊት ሰልፈኛ ለተሸለሙት ሰንደቅ ዓላማዎች ሰላምታ ሰጠ፡፡ ቀጥሎም በክብር ዘበኛ "የኢትዮጵያ መዝሙር" ሙዚቃ ተመታ፡፡"[29]

ተፈሪ ማርሽ በየትምህርት ቤቶች ጠዋት ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ ከብሔራዊ መዝሙሩ ቀጥሎ ይዘመር እንደ ነበር ዮሐንስ (፪ሺህ፬፤ 52) "ይህን መዝሙር [ማርሽ ተፈሪ] ተማሪ ቤት (አንደኛ ደረጃ) በነበርንበት ጊዜ "ኢትዮጵያ ሆይ ደስ ይበልሽ" በሚል ከሚጀምረው መዝሙር ጋር እንድንዘምር ይደረግ ነበር፡፡"በማለት ከገለጹት እንረዳለን፡፡ እሳቸው መዝሙሩን የዘመሩት በ1950ዎቹ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ይከታተሉ በነበረበት ጊዜ ነው፡፡ አሰናኙ በመጽሐፉ መቅድም ላይ ከገለጹት መረዳት እንደሚቻለው እስከ 1950ዎቹ ተፈሪ ማርሽ በትምህርት ቤቶች ከኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር ጋር ይዘመር እንደ ነበር መገንዘብ ይቻላል፡፡

ዘሪሁን አሰፋው በበኩላቸው፣ በቀድሞው ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ስታዲየም በግንቦት ወር 1960 ዓ. ም. በተከበረው የተማሪዎች የስፖርት በዐል ዘሪሁን ራሳቸው የሙዚቃ ጓዱ አባል እንደነበሩና ተፈሪ ማርሽን እንደዘመሩ ገልጸዋል፡፡ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ዓመታዊ የሰፖርት በዐል በሚከበርበት ቀን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በዐሉ በሚከበርበት በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ስታዲየም ሲደርሱ እሳቸውን ለመቀበል በወይዘሮ ስሂን አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሙዚቃ ጓድ (ማርሽ ባንድ) "ተፈሪ ማርሽ" መዘመሩን ገልጸዋል፡፡[30]

---

[29]ጽሕፈት ሚኒስቴር የጋዜጣና ማስታወቂያ ጽሕፈት ቤት በተለይ የወጣ፣ ብርሃንና ሰላም፣ ቁጥር ፲፩፣ ታኅሣሥ ፳፩ ቀን ፲፱፻፴፯፡፡

[30]ስለ ተፈሪ ማርሽ መዝሙር ምንነት ስንነጋገር ድንገት አስታውሰው የነገሩኝ ነው፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ግንቦት 12 ቀን 2008፡፡

ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው የዳግማዊ ምኒልክ፣ የልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንና የቅዱስ ጊዮርጊስ ትምህርት ቤቶች በክረምቱ ምክንያት ለእረፍት ከመዘጋታቸው በፊት የተሻለ ውጤት ያመጡ ተማሪዎችን ለመሸለም በየትምህርት ቤቶቹ ይደረጉ በነበሩ ዝግጅቶች ተፈሪ ማርሽ ይዘመር ነበር፡፡ ከዚኽም በላይ በመስቀል ደመራ ክብረ በዓል፣ የውጭ እንግዳን በመቀበል ሥነ ሥርዓት፣ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የልደት ቀን፣ የአማካሪ ምክር ቤትን ለመክፈት በተደረገው ዝግጅት ተፈሪ ማርሽ ይዘመር እንደ ነበር ከጋዜጦች ዘገባ ተመልክተናል፡፡ ተፈሪ ማርሽ በሚዘመርባቸው አጋጣሚዎች "የኢትዮጵያ ማርሽ" (የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር) ቀድሞ ወይም ዘግይቶ ይዘመር ነበር፡፡ አንዳንድ ጊዜ የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙርን ሚና ተፈሪ ማርሽ እንዲተካ የሚደረግበት አጋጣሚ ነበር፡፡ ተፈሪ ማርሽ ወጥነት ባለው መንገድ አገልግሎት አይሰጥም ነበር፡፡ አንዳንድ ጊዜ የአንድ ዝግጅት መርሐ ግብር ከመጀመሩ በፊት ሲዘመር ሌላ ጊዜ ደግሞ በመርሐ ግብሩ ማጠናቀቂያ ላይ ይዘመራል፡፡ በአንዳንድ ዝግጅቶች ተፈሪ ማርሽ መርሐ ግብሩ ሲጠናቀቅ ይዘመራል፡፡ በዝግጅቱ ቀድሞ የኢትዮጵያ ማርሽ ቀጥሎ ደግሞ ተፈሪ ማርሽ የሚዘመርበት አጋጣሚ አለ፡፡ ሌላ ጊዜ ደግሞ፣ ቀድሞ ተፈሪ ማርሽ ከተዘመረ በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር ይዘመራል፡፡ አልፎ አልፎ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር በሚዘመርበት አጋጣሚ ተፈሪ ማርሽ የማይዘመርበት ጊዜም ነበር፡፡ ይኽም በአንድ ዝግጅት ላይ ተፈሪ ማርሽ የሚዘመርበት የተወሰነ ጊዜ እንዳልነበረው ያስረዳል፡፡

ተፈሪ ማርሽ የሚዘመረው ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን (በኋላ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ) በተገኙባቸው አጋጣሚዎች ላይ ብቻ ነው፡፡ በጊዜው መዝሙሩ በተማሪ ቤት ምሥረታ ምረቃ ሥነ ሥርዓት፣ በክረምት ተማሪ ቤት ለዕረፍት በሚዘጋበት ዕለት፣ በመስቀል ደመራ በዓል ላይ በሚከናወን የወታደር ሰልፍ፣ በልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የልደት ቀን፣ የውጭ ሀገር እንግዳ በመቀበልና በሌሎችም ልዑል ዐልጋ ወራሽ በሚገኙባቸው ዝግጅቶች ላይ ይዘመር ነበር፡፡

መዝሙሩ ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንን አንድ ጊዜ በተውላጠ ስማቸው፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ በዓለም ስማቸው በመጥራት ያሞግሳል፤ ይመርቃል፤ የሀገር ሉዓላዊነት እንደሚያስጠብቁና ጥበብን ለሕዝብ እንደሚያወርሱ ያለውን ተስፋ ይገልጻል፡፡ ተፈሪ ማርሽ ስለ ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የሚያንፀባርቀውን ቀጥሎ በሚቀርበው ንዑስ ርእስ እንመለከታለን፡፡

#### 4) "ተፈሪ ማርሽ"፣ ማኅበረ - ታሪካዊ ዐውድ ትርጉምና ትንተና

በዚኽ ንዑስ ርእስ "ተፈሪ ማርሽ" የሚለውን መዝሙር ማኅበረ- ታሪካዊ ዐውዱን መሠረት በማድረግ እንተረጉማለን፤ እንተነትናለን፡፡ መዝሙሩን ለመተርጎምና ለመተንተን ተመሳሳይ ሐሳብ የሚያንፀባርቁትን ሥንኞች ተቆራኝተዋል፡፡ ለምሳሌ፣ የመዝሙሩ የመጀመሪያ ሥንኝ ለልዑል ዐልጋ ወራሽ ዕድሜ መርዘም ተማጽኖ የቀረበበት በመኾኑ ተመሳሳይ ይዘት ከሚያንጸባርቁት ከስድስት እስከ ዘጠኝ ከተደረደሩት ሥንኞች ጋር ተቆራኝቶ ተተንትኗል፡፡

መዝሙሩ የልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ዕድሜ እንዲረዝም ይመኛል፤ ይማጸናል፡፡ እሳቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሠሯቸውን መልካም ተግባሮች በመግለጽ ያሞግሳል፡፡ ኢትዮጵያን

ከወራሪ ጠላት ይጠብቃሉ፤ ነጻነትን ያስከብራሉ ጥበብን ያወርሳሉ ብሎ የማመንን ተስፋ ያስተጋባል፡፡ ዝርዝሩን ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

መዝሙሩ "እኛ" በሚል አንደኛ መደብ ብዙ ቁጥር አመልካች ተውላጠ ስም ራሳቸውን የጠሩ ዘማሪዎች መሪያቸውን "አንተ" በሚል ኹለተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ተባእታይ ፆታ በመጥራት ይጀምራል፡፡ መሪያቸውን "አንተ" በማለት መጥራታቸው ቅርበታቸውንና ፍቅራቸውን ይገልጻል፡፡ ዘማሪዎቹ በተለዋጭ ስም መሪያቸውን በመጥራት ለእነሱ ሲባል ዕድሜአቸው እንዲረዝምና እንዲኖሩላቸው "ኑርልን" በማለት ተመኝተዋል፡፡ ዘማሪዎቹ ዕድሜአቸው እንዲረዝም የተመኙላቸው መሪያቸው የዓለም ስም ተፈሪ[31] መኾኑን በስድስተኛው ሥንኝ ተገልጿል፡፡ "አንተ" በማለት የጠሯቸውን ሰው "ኑርልን መሪአችን እንበል አለልን" በሚለው ስንኝ መልካም የተመኙት፣ አንድም፣ ረጅም ዕድሜ እንዲኖሩ፣ ኹለትም፣ በመሪነታቸው በሥልጣናቸው እንዲቀጥሉ ነው፡፡ መሪያቸውንም በዓለም ስማቸው ወይም በሥልጣን ባላቸው ማዕረግ አልጠሯቸውም፡፡ ከዚኽ ይልቅ "መሪያችን" በማለት በገዥነታቸው፣ በአስተዳዳሪነታቸው ፣ በበላይ አዛዥነታቸው ጠርተዋቸዋል፡፡ ኹለትም፣ በመሪነታቸው ለኢትዮጵያ ከዚያም አልፎ ለአፍሪካ ባደረጓቸው መልካም ተግባሮች ነው፡፡ ለመሪያቸው ዕድሜ የተመኙበት ምክንያት የተገለጸው በሚከተሉት ሥንኞች ነው፡፡

(1) ኑርልን መሪአችን እንበል አለልን
(6) ተፈሪ መኰንን ሽህ ዓመት ኑርልን
(7) አኑረው ኦ. [!] ፈጣሪ ሕያው አርግልን
(8) ለዘለዓለም ተስፋ መመኪያ እንዲሆን
(9) ለወገኑ ሁሉ ለኢትዮጵያ በድፍን

በመጀመሪያው ሥንኝ መሪያቸው ለስንት ዓመት እንዲኖሩ እንደሚፈልጉ መዝሙሩ አይገልጽም፡፡ ዘማሪዎቹ በግልጽ መሪያቸው ለምን ያኽል ዓመት እንዲኖሩላቸው አይግለጹ እንጂ "ለኛ ኑርልን" ማለታቸው የተመኙላቸውን ዕድሜ ስንት እንደሚገመት ፍንጭ ይሰጣል፡፡ ዘማሪዎቹ በሕይወት እስካሉ ድረስ መሪያቸው በሕይወት እንዲኖሩላቸው መመኘታቸውን ከተማጽኗቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡ የመሪያቸው ዕድሜ "ለኛ ኑርልን" ባሉት ተማሪዎች ዕድሜ ልክ የተገደበ ነው፡፡ "እኛ" የሚለው ተውላጠ ስም ሌላን ትውልድ እንደማይወክል ልብ ይሏል፡፡

በስድስተኛው ሥንኝ ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ለሺሕ ዓመታት እንዲኖሩ ተመኝተዋል፡፡ ከመዝሙሩ ደራሲ ባሕልና እምነት መረዳት እንደሚቻለው የልዑል ዐልጋ ወራሺ ተፈሪ መኰንን

[31] መዝሙሩ ከቀረበበት ታሪካዊ ዐውድ መረዳት እንደሚቻለው መስከረም 17 ቀን 1909 ዓ. ም. ወይዘሮ ዘውዲቱ ምኒልክ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ተብለው ደጃዝማች ተፈሪ መኰንን ደግሞ ልዑል ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት ዐልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ተብለው ሥልጣን ያዙ (መርስዔ ኀዘን፣ 1999)፡፡ ዐልጋ ወራሽ አንዳንድ ጊዜ ራስ የሚለውን ጨምረው፣ ብዙውን ጊዜ ደግሞ ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት ዐልጋ ወራሽ ብቻ ተብለው ይጠራሉ፡፡ በዚኽ ጥናታዊ ጽሑፍ ተደጋግሞ የሚጠሩበትን ልዑል ዐልጋ ወራሽ የሚለውን መጠሪያ ተጠቅመናል፡፡

ዕድሜ እንዲረዝም ልመና የቀረበው ለልዑል እግዚአብሔር ነው፡፡ ሺሕ ዓመታት እንዲኖሩ የቀረበው ምኞትም ለልዑል ዐልጋ ወራሹ በማሰብ ብቻ አይደለም፡፡ ለመልካም ምኞት አቅራቢዎቹ ለራሳቸውም በማሰብ ነው፡፡ ይኸንንም "ኑርልን" በሚለው ቃል "አንተ ለእኛ ስትል ቆይልን" በማለት ገልጸዋል፡፡

ሺሕ ዓመታት እንዲኖሩ የቀረበው ምኞት የተጋነነና ለሰው ልጅ የተፈቀደ አይደለም፡፡ በእግዚአብሔር በረከት ሰው ረጅም ዕድሜ በሕይወት እንደሚቆይ በመዝ. 90፣ 16 "ረዥም ዕድሜን አጠግበዋለሁ፤ ማዳኔንም አሳየዋለሁ፡፡" ቢባልም የሰው ዕድሜ 70 ቢበዛ ደግሞ 80 ዓመታት ነው፡፡ በመዝሙሩ የቀረበው የዕድሜ ይርዘም ምክንያት "የዘመናችንም ዕድሜ ሰባ ዓመት ነው፤ ቢበዛ ሰማንያ ዓመት ነው፤ ከእነዚህ ቢበዛ ግን ድካምና መከራ ነው፤ የዋህነት ከእኛ አልፋለችና፣ እኛም ተገሥጸናልና፡፡" በማለት በመዝ. 80፣ 10 ከተነገረው ይቃረናል፡፡ ምኞቱ በክርስትና እምነት አስተምህሮ ሰው መኖር ይችላል ከተባለው ከፍተኛ ዕድሜ እጅግ የበዛ ነው፡፡ የልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ዕድሜ ሺሕ ዓመታት እንዲኾን የቀረበው ተማጽዕኖ የክርስትና እምነት አስተምህሮን ከመቃረኑም በላይ ምርቃኑ ለቀረበላቸው ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ድካምና መከራ የበዛበትን ሕይወት ይመኛል፡፡ ይኹን እንጂ፣ የመዝሙሩ ደራሲም፣ መዝሙሩ እንዲዘመር የፈቀደው አካልም ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን እንዲቸገሩ አስበውና አቅደው ያዘጋጁት ነው በማለት መተርጎም ያስቸግራል፡፡ አንድ ሰው መኖር የሚችለው የዕድሜ ጣሪያ እየታወቀ ሺሕ ዓመት እንዲኖሩ መመኘታቸው በዐማራው ባሕል የተለመደን ተግባር መፈጸማቸው ነው፡፡ ሺሕ ዓመት እንዲኖሩ መዝሙሩ ቢመኝም፣ ደራሲውም፣ ተመራቂውም ሊፈጸም እንደማይችል ያውቁታል፡፡ ይኹን እንጂ፣ መራቂው የማይፈጸምን ምርቃት መረቀ ተብሎ አይወቀስም፣ አይነቀፍም፡፡ ተመራቂውም የማይደርስ፣ የማይፈጸም፣ ቢፈጸም ድካምና መከራ የሚያስከትል ምርቃት በመመረቃቸው እንደ ለበጣ አይቆጥሩትም ወይም በክፉ ምኞትነት አይተረጉሙትም፡፡ ይልቁንም ምርቃቱን በበጎ ዐይን፣ በቅን ልቦና ይመለከቱታል፡፡ በባሕሉ የበዛ ዕድሜ ዕንዲኖሩ መመኘት ወይም መመረቅ ለመራቂውም፣ ለተመራቂውም ሥነ ልቦናዊ ደስታን ይፈጥራል፡፡ ልዑል ዐልጋ ወራሽ በመዝሙሩ ሺሕ ዓመታት እንዲኖሩ በቀረበላቸው ምርቃት ደስታን፣ ሥነ ልቦናዊ እርካታን ያገኙበታል እንጂ አይከፉበትም፡ ፡ መዝሙሩ የተመኙላቸውን ዕድሜ በአዎንታዊ ባይረዱት ኖሮ ለረጅም ዓመታት አገልግሎት እንዲሰጥ አይደረግም ነበር፡፡ መዝሙሩ "ሺሕ ዓመት ኑርልን" በማለት መመረቁ በባሕሉ በጎ ሥራ ለሠራ ወደፊትም ይሠራል ተብሎ እምነት ለተጣለበት መሪ ሊሰጠው የሚችለው መልካም ስጦታ መኾኑ ነው፡፡ ምርቃቱ በግነት እንደ ቀረበ ልብ ማለት አስፈላጊ ነው፡፡ ስለኾነም፣ በግነት ማቅረብና ስሜትን መግለጽ የደራሲውን ስሜት ለዘማሪው ወይም ለመዝሙሩ አድማጭ ማስተላለፍ፣ ማጋራት ተደርጎ ይተረጎማል፡፡

እግዚአብሔር ለልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን እጅግ የበዛ ዕድሜ እንዲሰጣቸው የቀረበው በተማጽዕኖ፣ በጩኸት፣ ድምፅን ከፍ አድርጎ በማሰማት፣ "ፈጣሪ ኾይ" በማለት፣ በቃል ኢጋኖ ነው፡፡ የቀረበው ምልጃም፣ በመዝሙሩ ሰባተኛ ሥንኝ "ኢ.[!] ፈጣሪ" በማለት ነው፡፡ ለፈጣሪ የቀረበው ልመና፣ ደጅ ጥናት ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ሕያው ይኹኑ በማለት ነው፡፡

ተማጽዕኖው፣ ልመናው፣ አንደኛ በሕይወት ይኑሩ፣ ኹለተኛ ዘላለማዊ ይኹኑ የሚል ነው። በሕይወት ይኑሩ የሚለው ምልጃ ስንት ዓመት እንዲኖሩ እንደ ተፈለገ አይገልጽም። ይኹን እንጂ፣ ምልጃውን ካቀረቡት ማለትም "እኛ" በሚል አንደኛ መደብ ብዙ ቁጥር አመልካች ተውላጠ ስም ከተጠሩት ሰዎች ፍላጎት አንጻር ከተረጎምነው ሕያው የሚለው በእነሱ ዕድሜ መጠን የሚለካ ነው። በመዝሙሩ እግዚአብሔር ለልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ረጅም ዕድሜ እንዲሰጣቸው ተማጽዕኖ የቀረበበት ምክንያት ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሠሯቸው መልካም ተግባሮች በመርካት፣ በመደሰት፣ ወደ ፊትም ለሀገር መልካም ሥራ ይሠራሉ ብሎ ተስፋ በማድረግ ነው። ስለኾነም የልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ዕድሜ እንዲረዝም ለፈጣሪ የቀረበው ልመና ለሀገራቸው የጀመሩት የልማት ሥራ እንዳይደናቀፍ ከማሰብ የመነጨ ነው። ይኽንንም በ"ብርሃንና ሰላም" ጋዜጣ፡-

> ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት ዐልጋ ወራሽ ረጅም ዕድሜ አግኝተው በዘመናቸው ኢትዮጵያ እንድትለማና እንደሚገባት እንድታድግ ተስፋችንና ምኞታችን ነው። ዕድሜ የሚያበዛ ሁሉንም እንደሚከናወን ማድረግ የሚቻለው አምላክ ነውና የኢትዮጵያ ተስፋ የሆኑት አልጋ ወራሻችንን ለኢትዮጵያ ልማትና ጽናት የሚሆን ዕድሜ ያጥግብልን ብለን አምላካችንን እንለምናለን።[32]

በማለት ከቀረበው መረዳት ይቻላል። መስከረም 1 ቀን 1918 ዓ. ም. የተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት አስተማሪዎችና ተማሪዎች በልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ቤት ተገኝተው አበባ ባበረከቱበት ዕለት፡-

> በርስዋ ውስጥ [በ1917 ዓ. ም. በተቋቋመችው ትምህርት ቤት] የዘሩትን የደግ ሥራ ዘር ፍሬ ወደሚለቀሙበት የመከር ጊዜ እንዲደርሱም ረጅም ዕድሜ እንመኝልዎታለን[።] ደግሞም ይኽን ብርሃን ባገራችን የሚያሰፋ ሥራን ያስጀመረዎ ኃይሉ የማይወሰነው አምላክ ብርሃኑ እየሰፋ እንዲሔድና ኢትዮጵያን ወደፍጹም ሥልጣኔ ደረጃ እንዲያደርሱዋት ልዕልናዎን እንዲጠብቅልን እየተማለልን ነው [።] ክቡራን ቤተ ሰዎችዎ ሁሉ ጋራ በረከትና ደስታ ሰላምም እንዲያድልልን እንለምነዋለን...[33]

በማለት የተናገሩት ለልዑል ዐልጋ ወራሽ ዕድሜ መለመን በወቅቱ ለኢትዮጵያ ዕድገት የሠሯቸውንና ወደፊት ይሠሯቸዋል ተብሎ በታመነው ላይ የተመሰረተ ነው። ስለኾነም፣ የልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ዕድሜ እንዲረዝም የፈለጉበት ምክንያት ሀገራቸውን የማልማት ተግባራቸው እንዲቀጥል፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ ምኞትና ክብር እንዲያስጠብቁ ከመፈለግ የመነጨ ነው።

[32] ብርሃንና ሰላም፣ መጀመሪ[ሪያ] ዓመት፣ ቁጥር ፴፩፣ ኀሙስ ሐምሌ ፳፫ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ. ም. የኢትዮጵያ መንግሥት ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የተወለዱበትን ቀን መታሰቢያ በዓል ምክንያት በማድረግ የተዘገበ ነው። ሐምሌ ፲፮ ቀን ፲፰፻፹፬ የተወለዱት ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በ፲፱፻፲፯ ዓ. ም. ፴፫ ዓመት እንደኾናቸው ተዘግቧል።
[33] ብርሃንና ሰላም፣ መጀመሪ[ሪያ] ዓመት፣ ቁጥር ፴፰፣ ኀሙስ መስከረም ፯ ቀን ፲፱፻፲፰ ዓ. ም. ክቡር ሐኪም ወርቅነህ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተናገሩትና አቶ ኤፍሬም ወደ አማርኛ የተረጎሙት ቃል ነው።

"ሕያው ይኹኑ" ለሚለው የተሰጠው ኹለተኛው ፍቺ ከስምንተኛው ሥንኝ ጋር ተቆራኝቶ ሲነበብ ዘላለማዊ ይኹኑ ማለት ይኾናል፡፡ ይኸም ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን እንዳይሞቱ፣ እግዜአብሔር ፍጻሜ የሌለው ዕድሜ እንዲሰጣቸው መማጸን ነው፡፡ እግዚአብሔር መጨረሻም፣ ፍጻሜም የሌለው ዘለዓለማዊ ዕድሜ ለልዑል ዐልጋ ወራሽ እንዲሰጣቸው የቀረበው ተማጽዕኖ ተፈጻሚነት የለውም፡፡ የኀጢአት ውጤት የኾነው የነፍስ ከሥጋ መለየት ለሰው ልጅ የተሰጠ ግዴታ ነው፡፡ ሞት ወደ ዓለም የገባው በአዳም አለመታዘዝ ምክንያት ስለመኾኑ "ስለዚህም በአንድ ሰው በደል ምክንያት ኀጢአት ወደ ዓለም ገባች፤ ስለዚችም ኀጢአት ሞት ገባ፤ እንደዚሁም ሁሉ ኀጢአትን ስለአደረጉ በሰው ላይ ሞት መጣ፡፡" በማለት በሮሜ. 5፣ 12 ተነግሯል፡፡ ስለኾነም፣ ለልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፍጻሜ የሌለው ዕድሜ እግዚአብሔር እንዲሰጣቸው በመዝሙሩ የቀረበው ተማጽዕኖ የክርስትና አስተምህሮን የሚቃረን ነው፡፡ ይኹን እንጂ፣ ምርቃኑ የቀረበው ቀደም ሲል እንደተገለጸው በግነት ይኹነኝ ተብሎና ታስቦበት የተነገረ ነው፡፡ ተማጽዕኖውን መረዳት የሚያስፈልገው በእግዚአብሔር ዘንድ ይፈጸማል ወይም አይፈጸምም ብሎ በመጠየቅና መልስ በመሻት ሳይኾን የታሰበውን መልካም ስሜት በመገንዘብ ነው፡፡ ከዚኽ አንጻር ግነቱ ስሕተት የለበትም፡፡ የተመራቂውን የልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንን ከሌላ ምናልባትም ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት አብልጦ ከማየትና ከፍ ያለ ዋጋና ግምት ከመስጠት የመነጨ ነው፡፡ ግነቱም በመዝሙሩ የተገለጸውን ስሜት ወደ ዘማሪውና አድማጩ ለማጋባት እንዲያስችል ታስቦ የቀረበ ነው፡፡[34]

ለኢትዮጵያ ሕዝብ ደስታን ያስገኙና እርካታን የፈጠሩ፣ ተስፋን ያሳደሩ የልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ተግባሮች በመዝሙሩ መንጸባረቃቸውን ከዚኽ በታች የተጠቀሱትን ሥንኞች በመመርመርና በመተንተን መረዳት ተገቢ ነው፡፡

(2) የኢትዮጵያ ፀሐይ ያፍሪካ ብርሃን
(3) ደማቅ በዓለሙ አብሪ ዙሪያውን
(4) ለሕዝቡም ሙቀቱ ትክክል ሚዛን
(5) መድኀኒት ለድውይ ፋና ለሕጻን

"የኢትዮጵያ ፀሐይ ያፍሪካ ብርሃን" የሚለው ሥንኝ የልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ተግባሮች ከተነገሩባቸው ሥንኞች መካከል የመጀመሪያው ነው፡፡ ተግባሮቻቸው የተነገሩትም ፀሐይ እና ብርሃን በሚሉ ኹለት ለዋጭ ዘይቤዎች ነው፡፡ በዘይቤዎቹ ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የፀሐይንና የብርሃንን ተፈጥሯዊ ባሕርያትና ተግባሮች ሙሉ በሙሉ ወርሰዋል። ፀሐይነታቸው ለኢትዮጵያ፣ ብርሃንነታቸው ደግሞ ለአፍሪካ ነው፡፡ ለዋጭ ዘይቤዎቹ የሚገልጹትን ለመረዳት የፀሐይንም፣ የብርሃንንም ተግባሮች መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ስለኾነም መጀመሪያ የፀሐይን ቀጥለን ደግሞ የብርሃንን ተግባሮች በመዘርዘር በመዝሙሩ በለዋጭ ዘይቤነት

[34] ብርሃኑ ገበየሁ (1999) <u>የአማርኛ ሥነግጥም</u> በሚል ርእስ ባሳተሙት መጽሐፍ ስለ ግነት ከገለጹት ለዚኽ ጥናት እንዲስማማ ተደርጎ የተወሰደ ሐሳብ ነው፡፡

የገለጹትን ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ለኢትዮጵያም፣ ለአፍሪካም ያከናወኗቸው በታሪክ ከሚታወቁ ተግባሮች ጋር እናነጻጽራለን፡፡

የፀሐይን ባሕርይ ለመግለጽ ተስማሚ ሙቀቷንና ብርሃኗን መሠረት ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ፀሐይ ለሰው ልጅ፣ ለእንስሳት፣ ለዕፅዋት ወዘተርፈ ተስማሚ ሙቀቷን እኩል ትለግሳለች፡፡ የሰው ልጅ የሚበላውን፣ የሚጠጣውንና አካላዊ ጤንነቱን የሚጠብቀው በፀሐይ ሙቀት ነው፡፡ ለአትክልትና ለዕፅዋት ካርቦንዳይ ኦክሳይድን ከሰዎች ለማግኘት፣ ሰዎችም ኦክስጂንን ከተክሎች ለማግኘት የፀሐይ ሙቀት ያስፈልጋል፡፡ ለእንስሳት ምግብ የሚኾነው ሣርና ቅጠላቅጠል የሚበቅለውና የሚያድገው በፀሐይ ሙቀት ነው፡፡ ለሰውነታቸው ተስማሚ የኾነው ሙቀት የሚገኘው ከፀሐይ ነው፡፡ ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሰው መመገብ የሚችሉት በፀሐይ ብርሃን ነው፡፡ የምንመገባቸው አእዋፋት፣ እንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶች፣ አትክልት፣ ጥራጥሬ፣ ፍራፍሬና ሥራሥር የፀሐይ ሙቀት ውጤቶች ናቸው፡፡ የፀሐይ ሙቀት ባይኖር ኖሮ የምንጠጣው ውሃ በረዶ ኾኖ መጠጣት በተቸገርን ነበር፡፡ የሰው ልጅ ከልጅነቱ ጀምሮ የፀሐይ ሙቀት ማግኘቱ ጤንነቱን ለመጠበቅ ያስችለዋል፡፡ መሬት ለኑሮ ምቹ የኾነችው የፀሐይ ሙቀት በመኖሩ ነው፡፡

የሰው ልጅ መጠለያውን ለመሥራት፣ ለሕይወቱ የሚያስፈልገውን ተግባር ለማከናወን (ለማምረት፣ ፍራፍሬ ለመልቀም፣ አውሬ ለማደን፣ መጠለያውን ለመሥራት ወዘተርፈ) የሚችለው የፀሐይ ብርሃን ጨለማን ድል በመንሣቱ ነው፡፡ ልዩ ልዩ ማኅበራዊ ግንኙነቶችን ለማድረግ፣ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመንቀሳቀስና የቦታ አቅጣጫን ለመለየት (አቅጣጫን ለማወቅ የሚያሥችል መሣሪያ ከመፈልሰፉ በፊት) የፀሐይ ብርሃን አስፈላጊም፣ ወሳኝም ኾኖ ቆይቷል፡፡ የሰው ልጅ ማኅበራዊ እንስሳ መኾን የቻለው የፀሐይ ብርሃን በመኖሩ ነው፡፡

ከላይ የተገለጸውን የፀሐይን ተፈጥሯዊ ባሕርይና የምታስገኘውን ጥቅም መሠረት በማድረግ ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን "የኢትዮጵያ ፀሐይ ናቸው" የሚለውን ዘይቤያዊ አገላለጽ መዝሙሩ የቀረበበትን ታሪካዊ ዐውድ መሠረት በማድረግ ተመርምሯል፡፡ ምርመራውን ለማካኼድም ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በሥልጣን ዘመናቸው ለሕዝቡ የፈጸሟቸው ተግባሮች በማስረጃነት ተጠቅሰዋል፡፡ ሥልጣኔንና ዕድገትን ለማምጣት፣ ዘመናዊ ዕውቀትንና ጥበብን ለማውረስ፣ ፍትሕን ለማስፈን፣ ኋላ ቀርነትን ለማስወገድ መጣራቸው፣ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና ነፃነት ለማስከበር መትጋታቸው በመዝሙሩ ተንፀባርቋል፡፡ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለማስከበርና ነጻነቷን ለመጠበቅ የልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ሚና ከፍተኛ ይኾናል የሚል እምነትና ተስፋ መኖሩን መዝሙሩ ያንጸባርቃል፡፡

የአፍሪካ ሀገሮች በቅኝ ግዛት ሥር በነበሩበት ጊዜ ለልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የፈረንሳይ ሪፑብሊክ መንግሥት ፕሬዚዳንት፣ የቤልጅክ ንጉሥ፣ የኢጣልያ ንጉሥ፣ የእንግሊዝ ንጉሥ፣ የግብጽ ንጉሥና የግሪክ ሪፑብሊክ ፕሬዚዳንት ሀገራቸውን እንዲጎበኙ ግብዣ መላካቸው ይታወቃል (ዘውዴ፣ 2006፤ መርስዔ ኀዘን፣ 1999)፡፡ ግብዣውን የተቀበሉበት ምክንያት ሀገሪቱ የምትቸገርበትን የንግድ ሥራና ከጋባዥ ሀገሮች ጋር ሊኖር የሚገባውን ወዳጅነት ለማጽናት ነው፡፡

በግብዣው መሠረትም ከአዲስ አበባ በባቡር ተሳፍረው ወደ ጅቡቲ ኼዱ፡፡ ከጅቡቲ በመርከብ ተሳፍረው ወደ ጋበዟቸው ሀገሮች ጉዞ አደረጉ፡፡ በዓለ ፋሲካን በኢየሩሳሌም አክብረው እስክንድሪያን፣ ፓሪስን፣ ብሩክሴልን፣ ሉክሰምበርግን፣ ስዊዲንን፣ ኢጣሊያን፣ ሎንደንን፣ ገኔቭን፣ አቴናን ጎብኝተው ነሐሴ 29 ቀን 1916 ዓ. ም. አዲስ አበባ ገቡ፡፡[35] በጉብኝታቸውም ከኢጣልያው መሪ ዱቼ ሞሶሊኒ ጋር በአሰብ ወደብ ነጻ የባሕር በር ስለማግኘት፣ ከእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር ጋር ስለ ጣና ባሕርና ስለ ወሰን ክልል ጉዳይ፣ ከፈረንሳይ ፕሬዚዳንት ጋር ስለ ምድር ባቡርና በጅቡቲ በኩል ነጻ የባሕር ወደብ ስለ ማግኘት፣ በግብጽ ከፓትሪያርኩ ጋር በኢየሩሳሌም ስላለው የኢትዮጵያ ገዳም ጉዳይ ተነጋግረዋል (መርስዔ ኀዘን፣ 1999)፡፡ የአውሮፓ ሀገሮች ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን እንዲጎበኟቸው መጋበዛቸው ለእሳቸውም፣ ለሀገራቸውም ይሰጥ የነበረው ክብር ከፍ ያለ እንደ ነበር ያስረዳል፡፡ በጉብኝታቸው ራሳቸውን ለዓለም አስተዋውቀዋል፤ ዝናን አትርፈዋል፡፡ የአውሮፓን ሥልጣኔ በኢትዮጵያ ለማስፋፋት የነበራቸውን ፍላጎት አጽንተዋል (ባሕሩ፣ ፪ሺህ)፡፡ ይኸንንም በአንደበታቸው "በአውሮፓ አገር በታላላቅ ተማሪ ቤት ብዙ ብዙ ተማሪዎች የሚማሩበት የሚያድሩበት እንደተሠራ አይቻለሁ፡፡ ይኸውም በዕውቀት መሣሪያነት ገንዘብ አገኝተው አሰፉትና ሠሩት እንጂ ምንም ሀሳብና ምኞቱ ታላላቅ ሥራ ለመሥራት ቢሆን ባንድ ጊዜ ለመፈጸም የሚቻለው የለም፡፡"[36] በማለት ከገለጹት መረዳት ይቻላል፡፡

ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ሥልጣኔን ለማምጣት ቁልፉ መሣሪያ ትምህርት ነው ብለው ያምኑ ስለ ነበር በ1915 ዓ. ም. ተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤትን ማስገንባት ጀመሩ፡፡ በ1916 ዓ. ም. አውሮፓን ለመጎብኘት ሲኼዱ የተማሪ ቤቱ ሥራ በፍጥነት እንዲፈጸም ትዕዛዝ በማስላለፍ አውሮፓን ጎብኝተው ሲመለሱ "ሥራው ከፍጻሜ ደርሶ አገኙት" (የተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት አጭር ታሪክ፣ ፲፱፻፵፪፤ ፯)፡፡ ኢትዮጵያን ለማዘመን ትምህርት ከፍተኛ ሚና አለው ብለው እንደሚያምኑ ተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤትን ሚያዝያ 19 ቀን 1917 ዓ. ም. በከፈቱበት ዕለት ከተናገሩት ቃል መረዳት ይቻላል፡፡ የተናገሩትም፡-

> ለኢትዮጵያ የምትደረጅበት ለመንግሥቷ ጽናት፣ ለሕዝቧ ድሎት የሚሆናት ዕውቀትን ፈልጎ አገኝቶ ሥራ መሥራት ነው፡፡ ሥራ ለመሥራት አስቀድሞ መሣሯን [መሣሪያን] ማበጀት ነው፡፡... ይህችንም የዕውቀት ምግብ ሰጥታ የምታሳድጋችሁን ተማሪ ቤት በጥበብ አድጋችሁ በአእምሮ በምትጎለምሱበት ጊዜ እግዚአብሔር እንደ እየእድላችሁ የሚሰጣችሁ ዕውቀት የሀገራችን መሣሯ [መሣሪያ] ናትና እንዳትጠብ እንዳትሰፋ እንዳትወድቅ እንድትበረታ እንድትረዱዋት እለምናችኋለሁ፡፡[37]

[35]ጽሕፈት ሚኒስቴር የጋዜጣና የማስታወቂያ ጽሕፈት ቤት፣ ስለ ዐምሳኛው የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የልደት በዓል መታሰቢያ በተለይ የወጣ፣ ብርሃንና ሰላም፣ ሐምሌ 16 ቀን 1934፤ ፲፡፡

[36] ብርሃንና ሰላም፣ መጀመሪ[ሪያ] ዓመት፣ ቁጥር ፲፱ ፣ ኅሙስ ሚያዝያ ፳፱ ቀን ፲፱፻፲፯፤ ፸፬፡፡

[37] ብርሃንና ሰላም፣ መጀመረ[ሪያ] ዓመት፣ ቁጥር ፲፱ ፣ ኅሙስ ሚያዝያ ፳፱ ቀን ፲፱፻፲፯፤ ፸፬፡፡

በማለት ነበር፡፡ በንግግራቸውም የሀገር ዕድገትን ለማምጣት መሣሪያው ትምህርት መኾኑን ተረድተው/ዐውቀው እንዲተጉ በዕለቱ ለነበሩት ተማሪዎች አደራ ሰጥተዋል፡፡[38]

ተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤትን በማቋቋም የጀመሩትን ሀገራቸውን የማዘመን ሥራ በተለያዩ ክፍለ ሀገሮች ተማሪ ቤቶችን እንዲቋቋም በማድረግ ተግብረዋል፡፡[39] ከዚኽም ፀሐይ ለሁብታምና ለድኻ እኩል ሙቀቷን እንደምትለግሰው ኹሉ ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ትምህርት ለኹሉም ኢትዮጵያውያን እንዲዳረስ ለማድረግ ከፍተኛ እንቅስቃሴ አድርገዋል፡፡ ትምህርት በዜጎች መካከል እኩልነትን ያስገኛል ብለው እንደሚያምኑም "የባላባት ልጅ የጌታ ልጅ ወገን አልሆነ ብላችሁ ልባችሁን ለትምህርት አታስንፉ ወገን ማለት ትምህርትና መታመን አገርን መውደድ ነው፡፡ ይህንን በልባችሁ ካሳደራችሁ እማስባችሁ እኔ ነኝ፡፡"[40] በማለት ከተናገሩት መረዳት ይቻላል፡፡

ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ኢትዮጵያ የዓለም መንግሥታት ማኅበር አባል እንድትኾን ሐሳቡን ከራሳቸው አመንጭተው አስበው ከወዳጅ ሀገሮች ጋር እየተጻጻፉ ተመካክረዋል፡፡ የመንግሥታቱ ማኅበር አባል ስትኾን ሀገራቸውን ማሻሻል የመሳፍንቱም፣ የመኳንንቱም ኀላፊነት መኾኑን አምነው በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ሰብሳቢነት ሐሳባቸውን በማቅረብ እንዲመከርበት አደረጉ፡፡ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ከመኳንንቱ ይኹንታን ሲያገኙ በሐምሌ ወር 1915 ዓ. ም. ለመንግሥታቱ ማኅበር በጻፉት ደብዳቤ ሀገራቸው አባል እንድትኾን ጠየቁ፡፡[41] ጥያቄአቸው ተቀባይነት በማግኘቱ በ1916 ዓ. ም. ኢትዮጵያ 52ኛ የመንግሥታቱ

---

[38] ትምህርት የሀገር ዕድገትን ለማምጣት ጠቃሚታ አለው ተብሎ መታመኑን ማኅተመ ሥላሴ (፲፱፻፳፩፤ ፳፻፺፱) "ርምጃችንን ወደ ሥልጣኔ ጎዳና ለመምራት ያስፈልግ የነበረ፣ ዛሬም ወደ ፊትም ልናደርገው የሚገባን፣ ልጆቻችን ጥበብን እንዲያፈሩ መጣጣር ነው፤ ይህም ካልተፈጸመ ማለት የሕክምና፣ የመሐንድስነት፣ የሕግ፣ የርሻ፣ የማዕድን፣ የልዩ ልዩ የጅ ጥበብ ሥራ ተማሪ ቤቶች ካልተከፈቱና ሕፃናት እንደ እኽልና እንደ ውሃ አስፈላጊያቸው የሆነውን ትምህርት ካላገኙ አገር ከከፍተኛ ሥልጣኔ ደረጃ ይደርሳል ብሎ ማሰብና መመኘት ዘበት ይሆናል፡፡" በማለት የተገለጸው ከልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ሐሳብ የተቀዳ ነው፡፡

[39] ዐልጋ ወራሽ ከኾኑበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. ባዲስ አበባ የተሠሩት ተማሪ ቤቶች፣ ፩ኛ የተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት፣ ፪ኛ የቅዱስ ጊዮርጊስ ተማሪ ቤት፣ ፫ኛ የቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ተማሪ ቤት፣ ፬ኛ የመድኀኔ ዓለም ተማሪ ቤት፣ ፭ኛ የእቴጌ መነን የሴት ተማሪ ቤት፣ ፮ኛ የቦይ እስካውት ተማሪ ቤት ናቸው፡፡ በያውራጃውና በየወረዳው ደግሞ ፯ኛ በጎንደር፣ ፰ኛ በጎዣም፣ ፱ኛ ባሌ፣ ፲ኛ በመቀሌ፣ ፲፩ኛ በሐረርጌ፣ ፲፪ኛ በጅጅጋ፣ ፲፫ኛ በድሬ ዳዋ፣ ፲፬ኛ በደሴ፣ ፲፭ኛ በጅማ፣ ፲፮ኛ በጎሬ፣ ፲፯ኛ በለቀምት፣ ፲፱ኛ በአርጆ፣ ፳ኛ ባምቦ (የእርሻ ተማሪ ቤት) እና ፳፩ኛ በሰላሌ ተመሥርተዋል (ማኅተመ ሥላሴ፣ ፲፱፻፳፪፤ ፺፻፪)፡፡

[40] ብርሃንና ሰላም፣ ሰባተኛ ዓመት፣ ቁጥር ፴፪፣ ኀሙስ ጥቅምት ፬ ቀን ፲፱፻፳፬፤ ፻፴፫፡፡

[41] በደብዳቤው ላይ እንደተገለጸው የመንግሥታቱ ማኅበር የሀገራቸውን ነጻነትና የግዛት አንድነት የሚያስከብርና የሚያረጋግጥ፣ በሀገሮች መካከል የሚኖረው ግንኙነት በሰላምና በመግባባት መኾኑን የሚቀበል እንደሚኾን ተስፋ አድርገዋል፡፡ ማኅበሩም ሀገራቸውን ከውጭ ጉልበተኛ ጥቃት ይታደጋታል ብለው እንደሚያምኑ ገልጸዋል፡፡ ከኢትዮጵያ የሚጠበቀውን የአባልነት ግዴታ ለመወጣትም ከተጠቀሰው ሐሳብ በተጨማሪ ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በመልእክተኞቻቸው በላኩት ደብዳቤ ኢትዮጵያ በመንግሥታቱ ማኅበር የተደነገገውን ለመቀበል ፈቃደኛ መኾኗን ገልጸዋል፡፡ ይኹን እንጂ፣ የመንግሥታቱ ማኅበር አባል ብትኾንም ሀገሪቱ ከማኅበሩ የጠበቀችውን ጥበቃ ማግኘት አልቻለችም፡፡ ይኽንን መገንዘብ የተቻለው ዘግይቶ ከ1928 ዓ. ም. የኢጣልያ ጥቃት በኋላ ነው፡፡ ግንዛቤአቸውንም "ማኅበሩ በሙሉ ፈቃዱና መላክተኞቻችን ስምምነቱን ፈርመው ተመለሱ፡፡ በአዲስ አበባም ትልቅ ደስታ ተደረገ፡፡ <u>ደስታም መደረጉ ዛሬ ኢጣልያ እንዳደረገችብን ከመሰለው አደጋ የማኅበሩ ቃል ኪዳን የሚጠብቀን</u>

ማኅበር አባል ሀገር ኾና ተመዘገበች፡፡ ይኽም ኢትዮጵያ ዓለም አቀፋዊ ዕውቅና እንድታገኝ አስችሏታል፡፡ ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ አድዋ ላይ ነጭን በጦርነት ማሸነፍ እንደሚቻል ያሳዩትን፣ ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በሰላም ከነጭ እኩል ማሰብና መሥራት መቻሉን አረጋገጠዋል፡፡ የዐድዋ ድል በዓለም በቅኝ ገዥዎችም፣ ተገዥዎችም የኢትዮጵያ ዝና ደምቆ እንዲታይና እንዲሰማ እንዳደረገው ኹሉ ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በጊዜው ኢትዮጵያን የመንግሥታቱ ማኅበር አባል ማድረጋቸው ራሳቸውንም ኢትዮጵያንም የሚያኰራ ተግባር ፈጽመዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ የፀሐይ ሙቀትና ብርሃን በፀሐይ ዙሪያ በምትሽከረከረው መሬት ለሚኖረው ሕዝብ በጠቅላላ እንደሚደርሰው ኹሉ፣ የእሳቸውም፣ የሀገራቸውም ዝና በየትኛውም የዓለም ክፍል ለሚኖረው ሕዝብ ታውቋል፤ ናኝቷል፡፡ የኢትዮጵያ የዓለም መንግሥታት ማኅበር አባል መኾን በአውሮፓ ሀገሮች ቅኝ ይገዙ ለነበሩ አፍሪካውያን ደግሞ የተስፋ ብርሃን እንዲፈነጥቅ የሚያደርግ ነበር፡፡ የመንግሥታቱን ማኅበር በግንባር ቀደምነት ከመሠረቱት ሀገሮች መካከል እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በአራቱም አቅጣጫዎች የሚያዋስኗትን ሀገሮች በቅኝ ይገዙ ነበር (ዘውዴ፣ 2006)፡፡ ኢትዮጵያ ግን ቅኝ ካለመገዛቷም በላይ የመንግሥታቱ ማኅበር አባል መኾኗ በዓለም የፖለቲካ መድረክ የነበራትን ከፍተኛ ቦታ ይገልጻል፡፡ እነዚኽ ሀገሮች ከመሠረቱት የመንግሥታቱ ማኅበር የኢትዮጵያ አባል መኾን የጥቁርን ከፍታ አሳይቷል፤ የማይቻል የሚመስልን እንደሚቻል አረጋግጧል፡፡ ሌሎቹ የመንግሥታቱን ማኅበር የመሠረቱት የአውሮፓ ሀገሮችም አብዛኛዎቹ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ቅኝ ግዛት ነበራቸው፡፡ በዚኽም የሚያስሞግሳቸውን ተግባር አከናውነዋል ማለት ነው፡፡

ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ግርማዊ ንጉሥ ተብለው የዘውድ ማዕረግ ከተቀበሉ በኋላ በ1921 ዓ. ም. በጥቂቶቹ የአውሮፓ ሀገሮች "የኢትዮጵያን ሌጋሲዮን" [ኢምባሲ] በማቋቋም የዲፕሎማሲ ግንኙነታቸውን ለማጠናከር ጥረት አድርገዋል፡፡ "ሌጋሲዮን" በመክፈት "ሚኒስትሮች" [አምባሳደሮች] ለመሾም የተወሰነው በእንግሊዝ ዋና ከተማ በሎንደን፣ በኢጣልያ ዋና ከተማ በሮማና በፈረንሳይ ዋና ከተማ በፓሪስ ነበር፡፡[42] ኢትዮጵያ በአውሮፓ ሀገሮች ኢምባሲዎችን ከመክፈቷ በፊት ኢጣልያ፣ ፈረንሳይ፣ እንግሊዝ በአዲስ አበባ ሌጋሲዮን በማቆም ሚኒስትሮችና ቆንስሎችም ሾመው ነበር (ዘውዴ፣ 2006)፡፡ የአውሮፓ ሀገሮች ቆንስላዎች በአዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ ቆንስላዎች ደግሞ በአውሮፓ መከፈት ኢትዮጵያ በዓለም የሚኖራትን ፖለቲካዊ ዕውቅና ከፍ ከማድረጉም በላይ በቅኝ ግዛት ሥር ለነበሩ አፍሪካውያን የተስፋቸው ማጽኛ ነበር ማለት ይቻላል፡፡

---

ስለ መሰለን ነበር እንጂ በሌላ ምክንያት አልነበረም፡፡" (ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጎ አድራጎት ድርጅት፣ ፲፱፻፳፭፤ ፶፮) (አጽንኦት የታከለ)፡፡

[42] ብርሃን ሰላም፣ አራተኛ ዓመት፣ ቁጥር ፴፫፣ ኅሙስ ጥቅምት ፲፰ ቀን ፲፱፻፳፩፡፡
በተጠቀሱት የአውሮፓ ከተሞች ኢምባሲዎች ከመከፈታቸው በፊት በ1890 ዓ. ም. በፈረንሳይ ቅኝ ግዛት ሥር በነበረችው ጂቡቲ፣ በ1892 ዓ. ም. ደግሞ በኢጣልያ ቅኝ ግዛት ሥር በነበረችው አሥመራ ተቀማጭ አምባሳደሮች ነበሩ (ኢትዮጵያ በአውሮፓ "ሌጋሲዮን" ስለከፈተችበት ጊዜ ስንነጋገር ሺፈራው በቀለ በ2013 ዓ. ም. ነግረውኛል፡፡ ቀኑን ግን አላስታውሰውም)፡፡

የኢትዮጵያ ፀሐይ የተባሉት ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ለአፍሪካ ሕዝብ ብርሃን መኾናቸው በመዝሙሩ ተንፀባርቋል፡፡ ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በቅኝ ግዛት ጨለማ ውስጥ ይገኙ ለነበሩት የአፍሪካ ሀገሮች ጨለማውን ለመግፈፍ የሚረዳ ብርሃን ፈንጥቀዋል፡፡ መዝሙሩ እንደሚገልጸው በኢትዮጵያ ከወጣችውና ከደመቀችው ፀሐይ የሚመነጨው ብርሃን የአፍሪካን ጨለማ ለመግፈፍ ረድቷል፡፡ ይኸም ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በኢትዮጵያ የሚፈጽሟቸው ተግባሮች አፍሪካውያን ነፃነታቸውን ለማስመለስ በሚያደርጉት ትግል እንዲበረቱ ተስፋቸው እንዲለመልም አድርጓል፡፡ የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና ነጻነት ለዓለም ሕዝብ ጎልቶ፣ በግ ብሎ፣ ደምቆ እንዲታይ ለማድረግ ጥረዋል፡፡ ሉዓላዊነቷ የተከበረችው ኢትዮጵያ አፍሪካን በቅኝ የሚገዙት ሀገሮች ከመሠረቱት የመንግሥታቱ ማኅበር አባል መኾን በጥቁርና በነጭ መካከል ከቆዳ ቀለም በስተቀር ልዩነት አለመኖሩን ለመገንዘብ ያስቻለ፣ ለኢትዮጵያ ኩራትን ያጎለመሰ፣ ለአፍሪካውያን ደግሞ ተስፋን ያጎለበተ ነበር፡፡ ብርሃን በዙሪያው የሚገኘውን ጨለማ እንደሚገፍፈው ኹሉ፣ ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በዓለምና በሀገራቸው የሚያከናውኗቸው ተግባሮች ለአፍሪካውያን የነጻነት ብርሃን እንዲታይ ረድቷል፡፡ ይኸም ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ለአፍሪካውያን ነጻነት ኢርቱዕ በኾነ መንገድ አስተዋጽኦ አድርገዋል ማለትን ይነግራል፡፡

አፍሪካውያን ከቅኝ ተገዢነት ነፃ እንደሚወጡ የተረዳው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት የውጭ ፖሊሲውን በማስተካከል ዲፕሎማቶቹ በዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ ፀረ-ቅኝ ግዛት ድምፆችን እንዲያሰሙ መደረጉ ለአፍሪካውያን ከተደረጉት መልካም ተግባሮች አንዱ ነው (Gebrekidan, 2012)፡፡ ለነፃነት የሚታገሉት የአፍሪካ ብሔራዊ ኮንግረስ አባሎችን፣ ለምሳሌ ኔልሰን ማንዴላ፣ ወደ አዲስ አበባ በማምጣት ሥልጠና እንዲሰጣቸው አድርገዋል (Mandela, 1994)፡፡ ነፃ የወጡ የአፍሪካ ሀገሮች የካዛብላንካ ቡድንና የሞኖሮቢያ ቡድን በመካከላቸው አንድ ዓይነት ትሥሥር ለመፍጠር ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ገለልተኛ አቋም በመያዝና ራሳቸውን "የአፍሪካ ቡድን" ብለው በመጥራት ኹለቱን ቡድኖች አቀራርበዋል፡፡ ቡድኖቹን ሊያግባባ የሚችል ሰነድ በማዘጋጀትና ወደ አዲስ አበባ በመጋበዝ ውይይት እንዲደረግበት በማድረግ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እንዲመሠረት አድርገዋል (Gebrekidan, 2012)፡፡ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሽልማት ድርጅት በአፍሪካውያን መካከል መቀራረብ እንዲጎለምስ ለማድረግም በአፍሪካ ላይ ጥልቅ ምርምር ለሚያደርጉ ሰዎች ሽልማት ይሰጥ ነበር[43] (የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሽልማት ድርጅት የተሻሻለው ሥርዓተ ቁመት፣ ፲፱፻፷፩)፡፡

[43]"የቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ሽልማት ድርጅት ስለ አፍሪካ ጥልቅ ምርምር ተሸላሚው ሰው ወይም የታወቀ አንድ ማኅበር ወይም ደግሞ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ያልሆነ ድርጅት በዜግነቱ፤ በዘሩ፣ በሃይማኖቱ፣ በቀለሙ፣ ልዩነትና በፖለቲካ፣ ዝንባሌው አስተያየት ሳይወሰድበት በህክምና፣ በእርሻ ፣ በከብት ጤና ጥበቃ፣ በሥነ ጥበብ፣ በኢንዱስትሪ፣ በኢኰኖሚ በማኅበራዊና በባህል ጉዳይ ላንድ የአፍሪካ አገር ሕዝብ ወይም አፍሪካውያን ሁሉ ሚጠቀሙበትን ዕውቀት በቅርብ ጊዜ ውስጥ በማበርከት፣ ለሽልማት ተገቢ ለሆነ ሰው ወይም ማኅበር በያመቱ ይሰጣል፡፡" (የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሽልማት ድርጅት የተሻሻለው ሥርዓተ ቁመት፣ ፲፱፻፷፩፣ አንቀጽ ፲፯ (፪) ሸ))፡፡

"ለሕዝቡም ሙቀቱ ትክክል ሚዛን" በሚለው ሥንኝ የመጀመሪያው ሐረግ የተፈሪ ተግባር የተገለጸው ሙቀት በሚል ለዋጭ ዘይቤ ነው፡፡ ዘይቤውን ለመረዳት የሙቀትን መገኛና ጥቅም በአጭሩ መግለጽ አስፈላጊ ነው፡፡ ሙቀት ከሰው ሠራሽ ነገሮችና ከተፈጥሮ ይገኛል፡፡ ሙቀትን ከሚሰጡ ሰው ሠራሽ ነገሮች መካከል እሳት፣ ኮረንቲ፣ ልብስና ቤት የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡ ፀሐይ፣ ፍል ውሃ (እሳተ ገሞራ) ሙቀት የሚገኝባቸው ተፈጥሮዎች ናቸው፡፡ ከሰው ሠራሽና ከተፈጥሮ የሚገኘው ሙቀት ለሰው ልጅ፣ ለእንስሳትና ለእጽዋት የተለያዩ ጥቅሞችን እንደሚሰጥ ቢታወቅም በሥንኙ ባለው ዐውዳዊ አጠቃቀም ዘይቤው የሚገልጸው የቅዝቃዜ ተቃራኒን ነው፡፡ ቀዝቃዛ በለዋጭ ዘይቤነቱ ያልደመቀ፣ ያልተሟሟቀ የሚል ፍቺ አለው፡፡ የተጎዳ፣ የተከፋ፣ የተጠቃ ስሜት ማለትም ይኾናል፡፡ በተቃራኒው ሙቀት የሚለው ቃል በዘይቤያዊነቱ ድምቀት፣ ደስታ፣ እርካታ ኩራት ማለትን ይልጻል፡፡ "ተፈሪ የሕዝቡ ሙቀት ናቸው" የሚለውም ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ደስታን፣ እርካታንና ሰላምን አስገኝተዋል፤ መከፋትንና መቆዘምን አስቀርተዋል ማለትን ይገልጻል፡፡ እነዚኽ የልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ተግባሮች ፍትሕንና መልካም አስተዳደርን ከማስፈን አንጻር ሊተረጎሙ ይችላሉ፡፡ ትርጉማቸውንም በሚቀጥሉት ገጾች እንመለከታለን፡፡

"ትክክል ሚዛን" በሚለው ኹለተኛው ሐረግ የልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ተግባር በለዋጭ ዘይቤ ተገልጿል፡፡ ዘይቤውን ለመረዳት የሚዛንን ተግባር ወይም አገልግሎት ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ በመኾኑም፣ ሚዛን የአንድን ነገር ክብደት ባለው አገልግሎት ሻጭና ገዢ ግብይታቸው ግልፅና የታወቀ፣ መተማመን ላይ የተመሠረተ እንዲኾን ያስችላል ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚኽ አገልግሎቱ መተማመንን ይፈጥራል፤ ሻጪም፣ ገዢም የሚስማሙበትን መረጃ ይሰጣል፤ ለአንደኛቸውም አያዳላም ተብሎ ይታመናል፡፡ ሚዛን በለዋጭ ዘይቤነቱ[44] ከአድሎና ከወገንተኛነት ነጻ የኾነን  ባሕርይ ይገልጻል፡፡ እንዲኽ ዓይነት ባሕርይ ያለው ሰው ትክክለኛ ፍርድ ይሰጣል፤ በሕግ መሠረት ይዳኛል፣ ውሳኔ ይሰጣል ተብሎ ይታመናል፡፡ ሚዛን በለዋጭ ዘይቤነቱ የአንድን ሰው ባሕርይና ተግባር ትክክለኛነት እንደሚገልጸው ኹሉ፣ በመዝሙሩ ባለው ዐውዳዊ አጠቃቀም ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በአስተዳደር ሥራቸውና ፍትሕ በመስጠት ተግባራቸው ትክክለኛ መኾናቸውን ለመግለጽ አገልግሏል፡፡ ዘይቤው እሳቸው የሚመሩትን፣ የሚያስተዳድሩትን ሕዝብ ኹሉንም እኩል ያዩታል፤ ፍትሕ አስፍነውለታል ወይም ያሰፍኑለታል ማለትን ያስረዳል፡፡ ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ ሕዝብ በሕግ መሠረት እንዲዳኝ፣ ትክክለኛ ፍትሕ እንዲያገኝ፣ ሕግ የሚጥሰውን፣ ሥርዓት የተላለፈውን በሕግ እንዲመራ አድርገዋል ወይም ያደርጋሉ ማለትን ይገልጻል፡፡

[44]ሚዛን በትእምርትነቱ ፍትሕንና አድሎ የሌለበት ዳኝነትን፣ ፍርድን፣ አስተዳደርን፣ የሕግ የበላይነትን ይወክላል፡፡ ፍትሕን ማስፈን በሕግ መሠረት መሥራትን፣ የሕግ የበላይነትን ማስገን ይገልጻል፡፡ ይኹን እንጂ፣ መዝሙሩ በተደረሰበትጊዜ ኢትዮጵያን ይመሩ የነበሩት ሥንግሥተ ነገሥታት ግርማዊት ዘውዲቱ ምኒልክም፣ ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንም ሥልጣናቸውን ከእግዚአብሔር እንዳገኙ ይቆጠር ስለ ነበር በሰው ከሚዘጋጀው ሕግ በላይ ነበሩ፡፡

*ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን መጋቢት 22 ቀን 1914 ዓ. ም. የተበየነበት ሰው ግልባጭ እንደጠየቀ እንዲሰጠው ደንብ አወጡ፡፡ ይኸውም "በናንተ ዳኝነት የሚነጋገረው ድኻ ተበየነብኝ ብሎ የተበየነውን ብይን ለማሳየት ሲመጣ እንደገና ባለጋራው ይምጣለት፤ የበየኑትም ዳኞች ይምጡለት እየተባለ ነገሩ ሳይቆረጥ ድኻም፣ ዳኞቹም የሚጉላሉ ስለሆነ ይህ እንዲቀር" የሚል ነው (ማኀተመ ሥላሴ፣ ፲፱፻፷፩፤ ፸፩)፡፡ ይኸን ደንብ ባለመተግበር ድኻው ለሚደርስበት መጉላላት ተጠያቂው ዋናው አገረ ገዥ ነው፡፡ ይኸም "ማንም ድኻ የተረታበት ወረቀት እንዲሰጠው ጠይቆ ሳይሰጠው ቀርቶ ባዶ እጁን የመጣ እንደሆነ ከባለጋራው ከሚነገርበት በቀር የመጣበት መንገድ የተጉላላበት ቀን ታስቦ የሚቆረጠውን መቀጫ የሚከፍል ዋናው አገረ ገዥው ነው፡፡" በማለት ተደንግጓል (ማኀተመ ሥላሴ፣ ፲፱፻፷፩፤ ፸፪)፡፡ ይኸም ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ይኸን ደንብ ማውጣታቸው "ድኻ ተበደለ፣ ፍርድ ጎደለ" ብለው ይሠሩ ነበር ማለት ያስችላል፡፡*

*ጥቅምት 21 ቀን 1921 ዓ. ም. ከልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ለፍርድ ሚኒስቴርና ለወንበሮች በተሰጠው ደንብ በየቀኑ የሥራ ተግባራቸውን የሚያከናውኑባቸው ሰዓቶች ተወስነዋል፡፡ ይኸውም "የፍርድ ሚኒስትሩና ወንበሮቹ ሁሉ ለሥራቸው ከጧቱ በ2 ሰዓት ገብተው እስከ ፯ ሰዓት ያስችላሉ፤ ከ፯ ሰዓት እስከ ፱ ሰዓት ዕረፍት ያደርጋሉ፤ ለማረፊያም በግቢ ለየራሳቸው ቦታ ይቀበላሉ፡፡ ከ፱ ሰዓት በኋላም በዚያው በየክፍላቸው አስችለው እስከ ፲፩ ሰዓት ቀላጤ ይሰጣሉ፡ ፡" የሚል ነው (ማኀተመ ሥላሴ፣ ፲፱፻፷፩፤ ፸፫)፡፡ የፍርድ ሥራ የሚከናወንበት ሰዓት በሕግ መወሰኑ በፍርድ ሚኒስትርና በወንበሮች በነ ፈቃድ እንዳይሠራ ያደርጋል፤ ፍትሕ ፈላጊዎች የሚያጋጥማቸውን መጉላላት ይቀንሳል፡፡*

*ተገቢውን የአስተዳደር ሥራ በመሥራት፣ ፍትሕንም በማስፈን ሕዝቡን ለማገልገል የአስተዳደርና የፍትሕ ተቋማትን መገንባትና ሥራው የሚመራበትን ሕግ ማውጣትን ይጠይቃል፡፡ ይኸን የተረዱት ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የአስተዳደር ተቋማት አብዝተው ገነቡ፡፡ በዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የተጀመረውን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችን የማቋቋም ሥራ አጠናከረው ከመቀጠላቸውም በላይ ለእያንዳንዱ ሚኒስቴር፣ ለአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤትና ለሐረር አውራጃ መሥሪያ ቤት ደንብ አውጥተዋል፡፡[45] ደንቡም በግለሰቦች ይኹንታና ግንዛቤ መሥራታቸው ቀርቶ ወጥ በኾነ መንገድ ሥራዎችን እንዲከናወኑ ረድቷል ተብሎ ይታመናል፡፡*

*ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ባሕልን መሠረት ያደረጉ ሕጎች እንዲቀሩ ወይም እንዲሻሻሉ አድርገዋል፡፡ ሌባ ሻይ (ሌባ ፈላጊ) ተብሎ የሚታወቀው ባህላዊ ሕግ እንዲቀር አድርገዋል[46] (መርስዔ ኀዘን፣ 1999፤ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በነ አድራጎት ድርጅት፣ ፲፱፻፷፩)፡፡ የአፍርሳታ ሕግም መጀመሪያ እንዲሻሻል፣ በኋላም እንዲቀር ተደርጓል (ባሕሩ፣ ፪ሺህ)፡፡ በቆየው የሕግ አፈጻጸም አንድ ሰው ነፍሰ ገዳይነቱ ሲረጋገጥ ለባለደሞቹ ተላልፎ እንዲሰጥና በገደለበት መንገድ*

[45] *ብርሃንና ሰላም፣ መጀመሪ[ሪያ] ዓመት፣ ቁጥር ፵፰፣ ኀሙስ ህዳር ፲፯ ቀን ፲፱፻፲፰፤ ፪፲፮-፪፲፰፡፡*

[46] ልጅ ኢያሱ "ከፍትሕ ይልቅ ለቂም መወጫና ደካማ ማጥቂያነት የሚያገለግለውን የሌባ ሻይ ሥርዓት መልክ ለማስያዝ ሞክሯል፡፡" (ባሕሩ፣፪ሺህ፤ 132)፡፡ ይኹን እንጂ፣ ሌባ ሻይ ሙሉ በሙሉ እንዲቀር የተደረገው ዘግይቶ፡፡

እንዲገደል ይደረግ ነበር፡፡ ይኽ ዓይነቱ ባሕላዊ የፍርድ አፈጻጸም እንዲቀርና በተወሰነ ቦታ እንዲገደል ወይም እንዲሰቀል ተደረገ (የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጎ አድራጎት ድርጅት፣ ፲፱፻፳፭)፡ ፡ ጥፋተኛ የተባለ ሰው ርስቱን እንዳይነቀል የሚከለክል ዐዋጅ ወጣ፡፡[47] ከረጅም ጊዜ ጀምሮ አገልግሎት ይሰጥ የነበረው ፍትሐ ነገሥት በ1923 ዓ. ም. በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ተተካ (ከፍትሐ ነገሥት በቀጥታ የተወሰዱ አንቀጾችም እንደተካተቱ ልብ ይሏል፡፡)፡፡ በዚኹ ዓመተ ምሕረት የመጀመሪያውን ሕገ መንግሥት በሥራ ላይ እንዲውል አደረጉ፡፡ የስልክ አገልግሎትም እንዲጀመር አደረጉ፡፡ "በ1924 ዓ. ም. በኢትዮጵያ ስም ባንክ አቆሙ፡፡"[48] ምንም እንኳ ማንኛውም ሕግ የሚጸድቀው በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቢኾንም በሀገሪቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የሕግ መወሰኛና የሕግ መምሪያ ክፍሎች ያሉት ፓርላማ እንዲቋቋም መደረጉ ክፍተኛ ርምጃ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ በወንጀለኛ በመቅጫ ሥነ ሥርዓት፣ በፍትሐ ብሔር፣ በፍትሐ ብሔር ሥነሥርዓት፣ በንግድና በባሕር ሕጎች እንዲተካ ተደርጓል፡፡ ለሕዝቡ ሚዛናዊ ወይም ትክክለኛ ፍርድ እንዲሰጥ ማድረጋቸው ለሕዝቡ ሰላምን እንዳስገኙ ይታመናል፡፡ ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንም ለሕግ ጥበቃ በማድረግ፣ ሲጣስም ቅጣትን በማስከተል የማኅበራዊ ግንኙነት መመሪያ የኾነውን ሕግ መጠበቅ፣ በሕግ መሠረት ጸጥታን ማስከበርና ሕዝቡን ከነጣቂ፣ ከዘራፊ፣ ከጉልበታም ለመጠበቅ ጥረት ማድረጋቸው በተጠቃሚው ዘንድ አስሞግሷቸዋል፡፡

የልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ተግባሮች "መድኀኒት ለድውይ ፋና ለሕፃን" በሚለው ሥንኝ በኹለት ለዋጭ ዘይቤዎች (መድኀኒት እና ፋና) ተገልጸዋል፡፡ መድኀኒት የሰው ልጅ በሥጋም፣ በመንፈስም ከማናቸውም ክፉትና ጉዳት ያድናል ወይም ይጠብቃል ወይም ይታደጋል (የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ 1989) ተብሎ ይታመናል፡፡ መድኀኒት በሥጋ ፈዋሽነቱ፣ አንድም፣ ከተለያየ ቅጠላቅጠል፣ ሥራ ሥር፣ ማዕድናት በእንክብል፣ በዱቄት፣ በፈሳሽ መልክ በመዘጋጀት ሕመምን ያድናል፤ ያሽራል፡፡ የሚያሽረውም በሥንኙ ድውይ በማለት የተገለጸውን የኅብረተሰብ ክፍል ነው፡፡ ድውይ የሚለው ቃልም ጤና ማጣትን፣ አቅመ ቢስ መኾንን፣ መሥራት አለመቻልን፣ ከሕይወት ወደ ሥጋ ሞት ማዘገምን ወይም መዳዝን ይገልጻል፡፡

የመዝሙሩ ደራሲ ዮፍታሔ ንጉሤ መንፈሳዊ ዕውቀታቸውን ተጠቅመው መድኀኒት የሚለውን ቃል ፍቺ ከመንፈሳዊ ታሪክ ጋር እንዲነጻጸር አድርገዋል፡፡ ይኸውም በመዝ. 43፣ 4 "አምላኬና ንጉሤ አንተ ነህ፤ ለያዕቆብ መድኃኒትን እዘዝ፡፡" የተባለውን፣ በኢሳ. 45፣ 21 "ከእኔም በቀር ሌላ አምላክ የለም፤ እኔ ጻድቅ አምላክና መድኀኒት ነኝ፤ ከእኔም በቀር ማንም የለም፡፡" በማለት እግዚአብሔር የእስራኤል መድኃኒት እንደተባለው ኹሉ ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንም በመዝሙሩ "ድውይ" [ድውያን] ተብለው ለተጠሩት ኢትዮጵያውያን መድኃኒት ተብለዋል፡፡ "በእግዚአብሔር እየተመራ እስራኤል ከጠላቶቻቸው እጅ ያዳነ ሰው ደግሞ አዳኝ ወይም ታዳጊ" እንደሚባል በመሳ. 3፣9 "የእስራኤልም ልጆች ወደ እግዚአብሔር ጮኹ፤ እግዚአብሔርም የሚያድናቸውን አስነሣላቸው፡፡"ተብሏል፡፡ በ2ነገ. 13፣ 5 "እግዚአብሔርም ለእስራኤል ታዳጊን

[47] ብርሃንና ሰላም፣ አራተኛ ዓመት፣ ቁጥር ፴፫፣ ኀሙስ ጥቅምት ፲፰ ቀን ፲፱፻፳፩፡፡
[48] ብርሃንና ሰላም ፣ ዘጠነኛ ዓመት፣ ቁጥር ፵፣ ኀሙስ መስከረም ፲፰ ቀን ፲፱፻፳፯፤ ፫፻፲፰፡፡

ሰጠ፤ ከሶርያውያንም እጅ ዳኑ፤ የእስራኤልም ልጆች እንደቀድሞው ጊዜ በድንኳናቸው ተቀመጡ፡ ፡" "ስለዚህ ለ[በ]ጠላቶቻቸው እጅ አሳልፈህ ሰጠሃቸው፤ አስጨነቋቸውም፤ በመከራቸውም ጊዜ ወደ አንተ ጮኹ፤ ከሰማይም ሰማሃቸው፤ እንደ ምሕረትህም ብዛት ታዳጊዎችን ሰጠሃቸው፤ ከጠላቶቻቸው እጅ ያዳኑአቸውን ታዳጊዎችን ሰጠሃቸው፡፡" (ነሀ. 9፣ 27) እንደ ተባለው ኹሉ ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን አቅመ ቢስ የኾኑትንና በልዩ ልዩ ምክንያት ራሳቸውን መርዳት የማይችሉ ሰዎችን (ባሪያዎችን) ነፃ ለማውጣት ጠንካራ ጥረት አድርገዋል፡፡

ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በኢትዮጵያ ዘመናዊ ትምህርት እንዲስፋፋ ማድረጋቸው መድኃኒት አስብሏቸዋል፡፡ በ1917 ዓ. ም. ተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት በማቋቋም መጀመራቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ ከማይምነት የማላቀቅ ጥረታቸውን መድኀኒት ለደካሞች እንደሰጡ ተቀጥሯል፡፡ ይኸንንም ኀሬ የቀዳማዊ ዐፄ ኀይለ ሥላሴ ትምህርት ቤት ለዕረፍት በሚዘጋበት ቀን አቶ ኀይለ ጊዮርጊስ ወልደ አማኑኤል ከተናገሩት ከሚከተለው ሐተታ እንረዳለን፡፡

> ትምህርት ማለት ያገር መድኃኒትና የሕዝብ ሕይወት ማለት ነው፡፡ ይኸውም ያገር መድኃኒትነቱ በትምህርት ዕውቀት አገር ከጉዳት የሚድንበትንና የሚለማበትን ይህን የመሰለውን በጎ ነገር ሁሉ ለመሥራት ይቻላልና ያገር መድኃኒት ሊባል ይገባል፤ የሰው ሕይወትነቱ ሰው በትምህርት በተሳለ አእምሮው የሩቁን አቅርቦ ለማሰብና ወደ ክፋትና ጥፋት ከሚያደርሰው ነገር በተቻለው እየተጠነቀቀ አስተውሎ መሥራት እግዚአብሔርን መፍራት በማወቁ ከእግዚአብሔር ሳይሆን በሌላ ረገድ በሚመጣበት ከልዩ ልዩ መከራ ይድንበታልና የሕዝብ ሕይወት ሊባል ይገባል፡፡[49]

ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በጦርነት ተማርከው ወይም በገንዘብ ተገዝተው ወይም ከሚኖሩበት አካባቢ በግድ ታፍነው ተወስደው በነጻ አገልግሎት ይሰጡ ለነበሩ፣ ሙብትና ነጻነት ላልነበራቸው፣ በተገዥነት ለሚኖሩ ባሪያ ይባሉ ለነበሩት ኢትዮጵያውያን ነጻነትን በዐዋጅ ሰጡ፡፡ በመጀመሪያ የባሪያ ንግድን በዐዋጅ ከለከሉ፡፡[50] መጋቢት 16 ቀን 1916 ዓ. ም. ባወጡት ዐዋጅ ደግሞ "ባሮች ቀስ በቀስ ነፃ እንዲወጡ" ደነገጉ (ባሕሩ፣ ፪ሺህ፤ 102)፡፡ ዐዋጁ ባሪያ መሸጥንና መግዛትን ይከለክላል፡፡ ዐዋጁ ከመውጣቱ በፊት የተገዙ ባሮች ነጻ የሚወጡበትን፣ ነጻ የወጡ ባሮች የሚተዳደሩበትንና ነጻነት ማግኘታቸውን የሚገልጽ ማስረጃ እንዴት እንደሚቀበሉ፣ ባሪያን የሚሸጡና የሚገዙ ሰዎች የሚቀጡበትን፣ የባሪያን ነጻነት ለመጠበቅ የሚሾሙትን ዳኞች ተግባርና መሥሪያ ቤቶች መቋቋምን ይደነግጋል (መርስዔ ኀዘን፣ 1999)፡፡

"ነፃ የወጡትን ባሮች ልጆች ሙያ አስተምሮ ራሳቸውን እንዲችሉ ለማድረግም ት/ቤት ተከፈተ፡፡ ትምህርት ቤቱን እንዲያስተዳድር የተመረጠው ከሕይወቱ አብዛኛውን ጊዜ ከእንግሊዞች ጋር

[49] ብርሃንና ሰላም፣ ዓሥረኛ ዓመት፣ ቁጥር ፴፯፣ ኀሙስ ጳጉሜን ፩ ቀን ፲፱፻፳፯፡፡

[50] "ኢትዮጵያ የዓለም መንግሥታት ማኅበር ለመግባት ደጅ እንድትጠና የተደረገችውም ገና ያልሰለጠነች የባሮችና የባርያ ፈንጋዮች ጉረኖ ናት በሚል ሰበብ ነበር፡፡" (ባሕሩ፣ ፪ሺህ፤ 101)፡፡

ያሳለፈውና ባርነትን በጽኑ ይቃወሙ ከነበሩት አንዱ ሐኪም ወርቅነህ" ነበሩ (ባሕሩ፣ ፪ሺህ፤ 102)፡፡ በሐኪም ወርቅነህ የተጀመረው ትምህርት ቤት ነፃ የወጡ ባሮችን በልዩ ልዩ የእጅ ሥራ በማሰልጠን ሥራ እንዲይዙ ተደረገ፡፡ ሐኪም ወርቅነህን የተኩት አቶ መንገሻ ከፈላ ትምህርት ቤቱ እንዲሻሻል አድርገዋል፡፡ ለምሳሌ፣ በ1927 ዓ. ም. በትምህርት ቤቱ ስልሳ የሚኾኑ ሴቶችና ወንዶች ልጆች በሸማ ሥራ፣ በአናጢነት ሥራ፣ በንባብና ጽሕፈት በጅምናስቲክም ይሠለጥኑ ነበር፡፡[51] ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ሕግ አውጥተው ባሮች ነፃ እንዲወጡ ማድረጋቸውን ለደካሞች መድኅኒት ናቸው በማለት ለመግለጽ ያስችላል፡፡

ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ለሕፃን ፋና መኾናቸው በተጠቀሰው ሥንኝ ተገልጿል፡፡ ይኸንን ዘይቤአዊ አገላለጽ ለመረዳት የፋናን ምንነትና አገልግሎት መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ፋና የሚለው ቃል ከጧፍ፣ ከፋኖስ፣ ከሻማ፣ ከችቦ፣ ከቅባ ኑግ፣ ከዘይት ወዘተርፈ የሚመነጭ መብራት፣ ብርሃን ማለት ነው፡፡ በአገልግሎቱም ሥጋዊና መንፈሳዊ ተግባራትን ለማከናወን ያስችላል፡፡ በመንፈሳዊ ተግባር፣ በቤተ መቅደስ የቅዳሴና የጸሎት ሥርዓትን ለመፈጸም አገልግሎት ለመስጠት ያስችላል፡፡ በሥጋዊ አገልግሎቱ ለረጅም ጊዜ በግለሰብ ቤትና ቤተ መንግሥት ልዩ ልዩ ሥራዎችን ለማከናወን በፋና መታገዝ የተለመደ ነበር፡፡ ፋና ማታ የሚቀርብን ማዕድ ዐይቶ ለምለሙን እንጀራ በወጥ አነካክቶ ለመብላት ምቹ ኹኔታ ይፈጥር ነበር፡፡ በጨለማ የተዋጠን ቦታ ለማየትና በጨለማ ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ ጭራሮን፣ የኮሸሽላን እንጨት ወዘተርፈ በአንድነት አሥሮ ችቦ በመሥራት ማብራት በኅብረተሰባችን ዘንድ የተለመደ ነበር፡፡ በገጠሩ የኅብረተሰብ ክፍል ዛሬም ፋና አገልግሎት መስጠቱን አላቋረጠም፡፡

ፋና ጨለማን እንደሚያስወግደው ኹሉ ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንም ሕፃናት ድንቁርናን፣ አለማወቅን አስወግደው ዕውቀትን እንዲያገኙ፣ ከድንቁርና ጨለማ ነጻ እንዲወጡ ማድረጋቸውን ከመዝሙሩ ታሪካዊ ዐውድና በ"ብርሃንና ሰላም"[52] ጋዜጣ ከተዘገበው መረዳት ይቻላል፡፡ ችቦን በፋናነት በመጠቀም በጨለማ ከሚያጋጥም እሾኽና እንቅፋት ራስን ማዳን እንደሚቻለው ኹሉ ሕፃናት በሕይወት ጉዟቸው እንቅፋት እንዳይገጥማቸው፣ የሕይወት ጉዟቸው የተስተካከለ እንዲኾን በትምህርት ተኮትኩተው፣ በዕውቀት በልጽገው እንዲያድጉ ምቹ ኹኔታ ፈጥረዋል፡፡ ፋና ማየት የሚገባን ቦታ ለማየት እንደሚያስችለው ኹሉ፣ ትምህርት ሕፃናት የወደፊት ሕይወታቸው የተቃና እንዲኾን ይረዳል፡፡ ለዚኽ ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ሕፃናት ዕውቀት እንዲቀስሙ ጥረዋል፤ የሕይወት መንገዳቸውን አሳይተዋል፡፡ እያንዳንዱ ለትምህርት የደረሰ ሕፃን ወደ ትምህርት ቤት እንዲኼድ የሚያስገድድ ሕግ አውጥተዋል፡፡[53] ዐዋጁም ወላጆች ዕድሜአቸው ከ7 እስከ 21 የደረሱ ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት በመላክ ንባብና ጽሕፈት ትምህርት፣ ለኑሯቸው፣ ለትዳራቸው ይኾነናል የሚሉትን የእጅ ሥራ (ሙያ)

[51] ብርሃንና ሰላም፣ ዓሥራ አንደኛ ዓመት፣ቁጥር ፳፬፣ ኀሙስ ግንቦት ፳፬ ቀን ፲፱፻፳፯፡፡

[52] ብርሃንና ሰላም፣ ዓሥረኛ ዓመት፣ ቁጥር ፴፯፣ ኀሙስ ጳጉሜን ፩ ቀን ፲፱፻፳፮፡፡

[53] ብርሃንና ሰላም፣ አራተኛ ዓመት፣ ቁትር ፴፫፣ ኀሙስ ነሐሴ ፲፰ ቀን ፲፱፻፳፩፤ ፫፻፴-፫፻፴፩፡፡

እንዲያስተምሩ ያስገድዳል፡፡[54] ይኸንን የማይፈጽሙ ወላጆች ሃምሳ ብር ቅጣት እንዲከፍሉ ይደነግጋል፡፡ የንስሐ አባቶች የንስሐ ልጆቻቸው ልጆቻቸውን እንዲያስተምሩ እንዲመክሩ፣ የገጠር መሪጌታዎች የንባብና የጽሕፈት ሥራ እንዲያስተምሩ፣ የደብር አለቆች ምእመናንን መንፈሳዊ ትምህርት እንዲያስተምሩ፣ ካላስተማሩ እንደሚቀጡ በዐዋጁ ተደንግጓል፡፡ በወላጆችና በቤተ ክህነት ሰዎች ላይ ግዴታዎችን የሚጥለውን ዐዋጅ ለማገዝም ትምህርት ቤቶች በተለያዩ ጠቅላይ ግዛቶች እንዲቋቋሙ ተደርጓል፡፡ ዐዋጁን በኹም የሀገሪቱ ክፍል ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ኹኔታ ተፈጥሮ ነበር ማለት ግን አያስችልም፡፡ ይኹን እንጂ፣ ለልጆች የቀለምና የእጅ ሥራ ትምህርት እንዲሰጥ ጥረት በማድረጋቸውና በአዲስ አበባና በአንዳንድ አውራጃዎችና ወረዳዎች ትምህርት ቤቶችን በማቋቋም ባመጡት ለውጥ በ"ተፈሪ ማርሽ" ተሞግሰዋል፡፡

ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የተሞገሱትና ረጅም ዕድሜ ልዑል እግዜአብሔር እንዲሰጣቸው ልመና የቀረበው ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሠሯቸው መልካም ተግባሮች፣ "ኢትዮጵያን ወደ ከፍታ አራምደዋል" በሚል ብቻ አይደለም፡፡ በመዝሙሩ እንደተንጸባረቀው ወደፊት ይሠሯቸዋል ተብለው ተስፋ በተሰነቀባቸው ጉዳዮችም ነው፡፡ ይኸም ሙገሳ ለተሠራው ዕውቅና መስጠት ብቻ ሳይኾን ይሠራል፣ ይፈጽማል ተብሎ ለሚታመነውም ነው (Burrow, 2008) ከሚለው ሐሳብ ጋር ይጣጣማል፡፡ ቀጥለው በተጠቀሱት ሥንኞች እንደተገለጸው በልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላይ ሕዝብ ተስፋ የጣለባቸው፣ አንደኛ፣ ኢትዮጵያን ከወራሪ ይጠብቃሉ፤ ኹለተኛ፣ ከፈጣሪ የተሰጣቸውን ስጦታ በመተግበር የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲሰለጥን፣ እንዲያውቅ ያደርጋሉ በማለት ነው፡፡ ከእነዚኽ ተስፋዎች በቅድሚያ ኢትዮጵያን ከወራሪ ይጠብቃሉ የሚል ተስፋ የተንፀባረቀባቸው ሥንኞች ቀጥሎ ይመረመራሉ፡፡

(10) ተፈሪ መኰንን ካላት ለኛ ሐበሻ
(11) የወራሪው የወራሪው ጠላት የግፍ ምኞት ዋሻ
(12) ተደፍኖ ይቀራል በተፈሪ ጋሻ

ከዚኽ በላይ በተጠቀሱት ሥንኞች የተገለጸውን ሐሳብ ለመረዳት ሐበሻ፣ ወራሪ፣ ጠላት፣ ግፍ፣ ምኞት፣ ዋሻ፣ ደፈነና ጋሻ የሚሉትን ቃላት ዐውዳዊ ፍቺ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ በሥንኝ ተራ ቁጥር ዐሥር ዐውዳዊ አጠቃቀም መሠረት ሐበሻ የሚለው ቃል ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የሚመሯት፣ የሚያስተዳድሯትና የሚጠብቋት ሀገር መጠሪያ ስም ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን እርስ በርስ ሲነጋገሩ ሐበሻ የሚለውን መጠሪያ እንደሚጠቀሙና "በገላጭ ቅጽልነቱም ኢትዮጵያዊ ከሚለው ይበልጥ ተመራጭ" መኾኑን ባሕሩ (፪ሺ፩) ገልጸዋል፡፡ "ሐበሻ ወይም በውጭ ትርጓሜው አቢሲኒያ የሚለው ቃል ከክርስቶስ ልደት በፊት ኢትዮጵያ ውስጥ ይገኙ ከነበሩት ነገዶች የአንዱ መጠሪያ ነበር ተብሎ ይገመታል፡፡" (ባሕሩ፣ ፪ሺ፩፤ 1)፡፡

[54]ለትምህርት የደረሱ ሕፃናት ወደ ትምህርት ቤት እንዲኼዱ የሚያስገድደው ዐዋጅ በዳግማዊ ምኒልክ የወጣው ሕግ ተከታይ ነው (ማኅተመ ሥላሴ፣ ፲፱፻፷፩፤ ፮፻- ፮፻፩)፡፡

ወራሪ የሚለው ቃል ሉዓላዊ የኾነችውን ሐበሻን/ኢትዮጵያን በሙሉ ወይም በከፊል በቁጥጥር ሥር ለማድረግ በጦር ኀይል የሚያጠቃ ወይም ያጠቃ ጠላት ማለትን ይገልጻል፡፡ ወራሪ የሚለው ቃል መደገሙ ሐበሻን በጦር ኀይል አጥቅቶ በቁጥጥሩ ሥር ለማድረግ የሚሻው ጠላት ለሚያደርሰው ወይም ለሚፈጽመው በደል፣ ክፉ ሥራ ትኩረት እንዲደረግ ይጋብዛል፤ ይጠይቃል፡፡ ጠላት የሚለው ቃል ደግሞ አንድም፣ በሥልጣን ይገባኛል ወይም በኢኮኖሚ ጥቅም የሚቀናቀን ባላጋራ፣ ባላንጣ ማለት ነው፡፡ አንድም፣ በአንድ መንግሥት የሚተዳደርን ግዛት ወይም በተወሰነ ጂኦግራፊያዊ ክልል የሚገኝን መሬት አጥቅቶ ለመያዝ የዘመተ ወራሪ ማለትን ይገልጻል፡፡ ሥልጣንን ወይም ኢኮኖሚያዊ ጥቅምን ለማስጠበቅ ኀይል መጠቀም፣ በአንድ መንግሥታዊ አስተዳደር ሥር የሚገኝ ግዛትን በከፊል ወይም በሙሉ ለመያዝ በማጥቃት በሌላው ላይ በደል ማድረስ፣ ክፉ መሥራት፣ ግፍ መፈጸም ነው፡፡ "የወራሪው የወራሪው ጠላት የግፍ ምኞት ዋሻ" በሚለው ሥንኝ እንደተገለጸውም ጠላት በሐበሻ ላይ በደል ለማድረስ ፍላጎት፣ ክጀላ አለው፡፡ በሐበሻ ላይ ለማድረስ የሚፈልገው የበደል ደረጃም የከፋና ከባድ ነው፡፡ ይኸ የተገለጸው ዋሻ በሚለው ቃል ነው፡፡ ቃሉ በቁሙ በተፈጥሮ ወይም በሰው ወይም በአውሬ የተቆፈረ ጎሬ ወይም ጉድጓድ ነው፡፡ በጥልቀት ወደ ታች የተሰረጎደ መሬትን የሚገልፀው ቃል የግፍ ምኞት ከሚለው ሐረግ ጋር ተቆራኝቶ ሲተረጎም ጠላት ለመፈጸም የሚያቅደውን የከፋ ድርጊት ደረጃ ይገልጻል፡፡

ይኹን እንጂ፣ ራሳቸውን "እኛ" ብለው የሚጠሩ ኢትዮጵያውያን ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ሐበሻን በወራሪ ጠላት እንዳትደፈር ያደርጋሉ፣ ይታደጋሉ ብለው እንደሚያምኑ ተገልጿል፡፡ በግፍ ተነሥቶ፣ የጦር ኀይል አዝምቶ ሐበሻን ለማጥቃት የሚፈልግ ጠላት ያሰበውን አያሳካም፣ ይልቁንም በልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ይጠቃል፣ ይገደላል፣ ይቀበራል፡፡ ጋሻአገልግሎት መረዳት እንደሚቻለው፣ ሐበሻን አጥቅቶ በቁጥጥሩ ሥር ለማድረግ ወይም ዘርፎ ለመኼድ ምኞት፣ ጉጉት ያለውና ሙከራ የሚያደርግ ጠላት መጀመሪያ ይመከታል፤ ቀጥሎ ይጠቃል፡፡

ጋሻ የሚለው የጦር መሣሪያ በመዝሙሩ የሚገለጸው፣ አንድም፣ በተደረሰበት ወቅት ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ጠላትን ለመመከትና ለማጥቃት የሚችሉት በተለመደው ባሕላዊ ጦር መሣሪያ ነው ማለትን ይገልጻል፡፡ ይኸም በዘመናዊ ጦር መሣሪያ ሀገርን ከጠላት መከላከል ብሎም ማጥቃት የሚለው ግንዛቤ አለመስረጹንና ዘመናዊ የውትድርና አደረጃጀት አለመኖሩን ይጠቁማል፡፡ ይልቁንም ተፈሪ ማርሽ የተደረሰው ከዐድዋ ድል 30 ዓመታት በኋላ በመኾኑ በብዙ ኢትዮጵያውያን ዘንድ፣ መዝሙሩን በደረሱት ሰው ጭምር ትዝታው ከአእምሮ አልጠፋም ተብሎ ይታመናል፡፡ ዐድዋ ላይ በተገኘው ድል ጋሻ የነበረውን አገልግሎት ያስታውሳል፡፡ አንድም፣ ጋሻ ኀይልን፣ ጉልበትን ይገልጻል፡፡ ይኸም ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ሀገራቸውን ከጠላት ጥቃት የሚመክትና ድል ማድረግ የሚችል ጦር አደራጅተዋል ማለትን ይገልጻል፡፡ ይኸም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከኾኑ በኋላ ዘመናዊ ጦር ለማደራጀት ያደረጉትን ጥረት ያስታውሳል፡፡ የኢትዮጵያን ጦር ለማዘመን ከፍተኛ እንቅስቃሴ ቢደረግም ሀገርን ለመታደግ የሚችል ወታደራዊ አቅም መፍጠር እንዳልተቻለ በ1928 ዓ. ም. የኢጣልያ ጦር የፈጸመው ጥቃት ማስረጃ ነው፡፡

በልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ኀይልና ብርታት እምነቱ የጸናው የሐበሻ ሕዝብ ሌላ ተስፋ ሰንቋል፡፡ ተስፋውም ብልሃት፣ ዕውቀትና ዘዴ ያስገኙልናል የሚል ነው፡፡ ይኸም በሚከተሉት ሥንኞች ተገልጿል፡፡

(13) ተፈሪ እያለልን አንጠራጠርም
(14) ከነዓን ጥበብን ሳንወርሳት አንቀርም
(15) ለሰ[ስ]ማችን ሞገስ ለደጉ ተፈሪ
(16) ጥበብ ተሰጥቶታል ከላይ ከፈጣሪ

ከዚኽ በላይ በተጠቀሱት ሥንኞች የተነገረውን ቅኔያዊ መልእክት ለመረዳት በቅድሚያ በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ከነዓን የተነገረውን ታሪክ በአጭሩ መግለጽ አስፈላጊ ነው፡፡ በዘፍ፣ 10፣ 6፣ 18-19 እንደተነገረው ከነዓን የካም የልጅ ልጆች ይኖሩበት የነበረ ሀገር ነው፡፡ ከነዓን ለአብርሃምና ለዘሩ ትሰጣለች በማለት እግዚአብሔር በተናገረው (ዘፍ. 12፣ 7) መሠረት በባርነት ይኖሩ የነበሩት የኤስራኤል ልጆች በሙሴ መሪነት ከግብፅ ወጥተው ወደ ከነዓን ኼዱ፡፡ ሙሴ በሠራው ስሕተት ወደ ከነዓን እንዳይገባ በመከልከሉ (ዘኁ. 20፣ 1-13፤ መዝ. 105፣ 32፡33) ኢያሱ እስራኤላውያንን መርቶ ወደ ከነዓን እንዲኼድ አደረገ (ዘኁ. 27፣ 12-23)፡፡ ኢያሱም እስራኤላውያንን መርቶ ወደ ከነዓን በመውሰድ ምድሩን አወረሳቸው (1 ዜም. 7፣ 26፣ 27፤ ዘኁ. 1፣ 4-10)፡፡ እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብጽ ባርነት አውጥቶ እስከ ዮርዳኖስ ድረስ ለማድረስ ሙሴን መሪ አደረገ፤ ሙሴም ኢያሱንም እስራኤላውያንን ወደ ከነዓን መርቶ እንዲወስድ አደረገ፡፡

ከነዓን የሚለው የሀገር ስም ሲጠራ፣ ሙሴ፣ እስራኤላውያንና ነፃነት የሚሉት ይታወሳሉ፡፡ በእዚኽ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክና የታሪክ ተዋናዮች የመዝሙሩ ቅኔያዊነት ተነግሯል፡፡ ቅኔያዊነቱ የተነገረው ሙሴንና ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንን፣ እስራኤላውያንንና የኢትዮጵያን ሕዝብ፣ ከነዓንንና ጥበብን በማነጻጸር ነው፡፡ ሙሴ እስራኤላውያንን ከግብጽ ባርነት አውጥቶ ሀገራቸው ወደ ኾነችው ከነዓን በመውሰድ እንዳወረሳቸው ኹሉ፣ ተፈሪም የኢትዮጵያን ሕዝብ ከኋላ ቀርነት፣ ከድንቁርና ከማይምነት ነጻ አውጥቶ ጥበብ እንደሚያወርስ ተስፋ ተደርጓል፡፡ እንደዚኹም፣ ሙሴ እግዚአብሔር ተገልጦለት እስራኤላውያንን ከባርነት ነጻ እንዳወጣቸው ኹሉ፣ ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንም የኢትዮጵያን ሕዝብ ከኋቀርነት፣ ከድንቁርና ነፃ ለማውጣት ከፈጣሪ ጥበብ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ይኸም የሰው ልጅ በምድር ሲኖር አእምሮው በፈቀደለት ከሚደርስበት ምድራዊ ዕውቀት ይበልጣል ማለትን ይገልጻል፡፡

**5) ማጠቃለያ**

"ተፈሪ ማርሽ" የሚለው መዝሙር "ማርሽ ተፈሪ" እየተባለም ይጠራል፡፡ በዐማርኛ ዘመናዊ መዝሙር ታሪክ የመጀመሪያው ነው፡፡ መዝሙሩ ከርእሱ ጀምሮ ጠቅላላው ይዘቱ ሲመረመር ለልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያሞግሳል፡፡ እሳቸው ያከናወኗቸውንና ሊያከናውኗቸው ይችላሉ የተባሉ ተግባሮችን ይዘረዝራል፡፡ የደካሞች ዋቢ፣ የኢትዮጵያ ዕድገት መሪ፣ የሕፃናት

መብራት፣ የአፍሪካ ተስፋ፣ የፍትሕ ጠበቃ፣ የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና ነጻነት አለኝታ፣ የጥበብ አባት፣ የፈጣሪ መልእክተኛ መኾናቸውን በመዘርዘር ተወድሰዋል፡፡ ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ለሕዝባቸው ዕውቀት በማውረሳቸው፣ ሀገራቸውን ለማዘመን በመጣራቸው፣ ጠላትን ለመመከትና ለማጥቃት እንደሚችሉ በመታመናቸው፣ ጥበብን ለማጎናጸፍ ተስፋ በመስጠታቸው በመዝሙሩ ተሞግሰዋል፡፡ የሠሯቸውንና ወደፊትም ይሠሯቸዋል የተባሉ ብሔራዊና አህጉራዊ ተግባሮች በማሰብ ረጅም ዕድሜ እንዲሰጣቸው፣ ዘላለማዊ፣ ሕያው እንዲያደርጋቸው መዝሙሩ ለፈጣሪ ተማጽእኖ ቀርቦላቸዋል፡፡

ከመዝሙሩ ማኅበረ-ታሪካዊ ዐውድ መረዳት እንደሚቻለው በመዝሙሩ ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የተሞገሱባቸው ተግባሮች የተፈጸሙ ናቸው፡፡ ባርነትን የሚከለክል ሕግ አውጥተው ተግብረዋል፡፡ የፍትሕ ሥርዓቱንና አፈጻጸሙን አሻሽለዋል፡፡ በዚኽም ነፍስ የገደለን ሰው የፍርድ አፈጻጸም ለውጠዋል፡፡ ጥፋተኛ የተባለ ሰው ከርስቱ እንዲነቀል ይደረግ የነበረውን አሻሽለዋል፡፡ ወንጀለኛን ለማወቅና ለማግኘት ይሠራበት የነበረው ባሕላዊ የሌባ ሻይ ሕግ ንጹሕን ከጥፋተኛ መለየት የማያስችል በመኾኑ እንዲቀር አደርገዋል፡፡ የአፍርሳታ ሥርዓት ሕዝቡን ሥራ የሚያስፈታና ለእንግልት የሚዳርግ ወንጀለኛንም በእርግጠኝነት ለመለየት የማያስችል በመኾኑ በመጀመሪያ እንዲሻሻል፣ በኋላም እንዲቀር አድርገዋል፡፡ የአውሮፓ ሀገሮችን በመጎብኘት ሀገራቸውን የማበልጸግ ሕልማቸውን ከፍ አድርገዋል፡፡ የመንግሥታቱ ማኅበር አባል በመኾን የራሳቸውንና የሀገራቸውን ዓለም አቀፋዊ ዕውቅና እንዲኹም የሉዓላዊነትና የነጻነት ትእምርት የኾነችውን ሰንደቅ ዓላማ ከፍ አድርገዋል፡፡ ይኸም በቅኝ ግዛት ይማቀቁ ለነበሩ አፍሪካውያን ነፃ ለመውጣት የነበራቸውን ሕልም እውን ለማድረግ እንዲተጉ፣ ተስፋቸው እንዲለመልም፣ ለተግባራዊነቱ እንዲነሣሡ አድርጓቸዋል፡፡ በዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ የተጀመሩትን ሥራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ አድርገዋል፡፡ በዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ የተጀመረውን ዘመናዊ ትምህርት ቤት የማቋቋም ሥራ በመከተል በአዲስ አበባና በተለያዩ ጠቅላይ ግዛቶች ትምህርት ቤቶች አቋቁመዋል፡፡ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችን ቁጥር ጨምረዋል፤ አዳዲስ መሥሪያ ቤቶችንም አቋቁመዋል፡፡ ለእያንዳንዳቸው ሥራቸውን የሚመሩበት ደንብ በማውጣት የአስተዳደር ሥራቸው የቀለጠፈና አንድ ወጥ እንዲኾን ተደርጓል፡፡ የኅትመት ሥራ እንዲጠናከር የማተሚያ መሣሪያ ከውጭ ሀገር አስመጥተዋል፡፡ በዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ የተጀመረው የጋዜጣ ኅትመት ለማስቀጠል በመጀመሪያ "ብርሃንና ሰላም"፣ በኋላ ደግሞ "ከሣቴ ብርሃን" የተባሉ ሳምንታዊና ወርሐዊ ጋዜጦች አቋቁመዋል፡፡ በመኾኑም ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የተጠቀሱትን ተግባሮች ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንደፈጸሙና እንደሚፈጽሙ በማመን በመዝሙሩ ተሞግሰዋል፡፡ ከመዝሙሩ ማኅበረ - ታሪካዊ ዐውድ መረዳት እንደሚቻለው የልዑል ዐልጋ ወራሽ ተግባርና በመዝሙሩ የተንጸባረቀው ይዘት ይጣጣማሉ፡፡

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ እያሉ ለሀገሪቱ የተሠሩት ሥራዎችና ወደፊትም የሚሠሩት በልዑል ዐልጋ ወራሹ እንደተከናወኑ ተደርገው በመዝሙሩ ለምን ተንጸባረቁ? ለሚለው ጥያቄ መልስ መስጠት ታሪካዊ እውነታውን ለመረዳት ያስችላል፡፡ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱም፣ ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪም የሥልጣን ግንኙነት ወደ ሥልጣን ከወጡበት ዕለት

ይጀምራል፡፡ ዘውዲቱ ከፋሌ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ ተደርገው የአባታቸውን ዙፋን እንዲወርሱ ሲደረግ ደጃች ተፈሪ መኰንን ደግሞ ዐልጋ ወራሽ ተባሉ፡፡ "ተፈሪን ዐልጋ ወራሽ ያደረገው የፖለቲካ ለውጥ...የእንግዳነት፣ የተገላቢጦሽነትና የአደናጋሪነት ባሕሪ ነበረው፡፡ እንግዳነቱ ከዚያ በፊት ንጉሡ ዘውድ ሲጭን ወይም ንግሥቲቱ ዘውድ ስትጭን አልጋ ወራሹን መሰየም የተለመደ ስላልነበረ ነው፡፡" (ባሕሩ፣ ፪ሺህ፤ 139)፡፡ ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ በነበራቸው የተሻለ የፖለቲካ ልምድና ብስለት ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ በመባል የሀገሪቱን ሥልጣን ጠቀለሉ (ባሕሩ፣ ፪ሺህ)፡፡ በሀገሪቱ በሚከናወኑ ፖለቲካዊ ጉዳዮች የልዑል ዐልጋ ወራሹ የወሳኝነት ሚና የጎላ ኾነ፡፡ ተፈሪ ማርሽ በሚለው መዝሙር የልዑል ዐልጋ ወራሹ ማንነት ጎልቶ የመደመጡ ምክንያት ይኸው የፖለቲካ ሥልጣን ጉልበታቸው ነበር፡፡ ለንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ እንደ ተዘመረ[55] ቢነገርም መዝሙሩ የእሳቸውን ሰብእና እንዴት እንደሚገልጽ ለመረዳት መዝሙሩን ማግኘት አልተቻለም፡፡ ስለ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ የተዘመረውን መዝሙር መፈለግና ይዘቱን መመርመርና ለልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ከተዘመረው ተፈሪ ማርሽ ጋር ማነጻጸር በታሪክ የሚታወቀው የኹለቱ የሥልጣን ክፍፍል እንዴት አንደተገለጸ ለመረዳት ያግዛል፡፡ ለዚኽም ተመራማሪዎች ትኩረት ቢሰጡ መልካም ነው፡፡

ተፈሪ ማርሽ ከኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር ቀድሞ እንደተደረሰ ቢታወቅም ስለአገልግሎቱ በተሟላ መንገድ ለመረዳት አልተቻለም፡፡ በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ እንደተዘገበው አገልግሎቱ አንድ ወጥ አልነበረም፡፡ ተፈሪ ማርሽ አገልግሎት መስጠት ከጀመረ በኋላ የተዘጋጀውን የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙርን ተክቶ አገልግሎት የሰጠባቸው አጋጣሚዎችም እንደ ነበሩ መገንዘብ ተችሏል፡፡ ይኽ አገልግሎቱ ከ1933 ዓ. ም. እንዴት እንደቀጠለ ለመረዳት የተለያዩ ጋዜጦችን፣ መጽሔቶችንና መጻሕፍትን በመመርመር መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡ ይኽም ተመራማሪዎች በመዝሙሩ ላይ ተጨማሪ የምርመር ትኩረት ማድረግ ይሻል፡፡

[55] የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት በክረምቱ ምክንያት ለዕረፍት በሚዘጋበት ሐምሌ ፲፩ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ. ም. ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን፣ ከቡራን መኳንንትና ወይዛዝርም የተሻለ ውጤት ያመጡ ተማሪዎችን ለማበረታታት ሽልማት በሚሰጡበት ቀን በትምህርት ቤቱ ተገኙ፡፡ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱም ልዑል ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን እንዲኹም አጅበዋቸው የኼዱት እንግዶች በተዘጋጀላቸው ቦታ እንደተቀመጡ ተማሪዎቹ "የኢትዮጵያን መዝሙር" ባማረ ዜማ ዘመሩ፡፡ ሽልማቱ ከተሰጠና የተለያዩ ዝግጅቶች ከቀረቡ በኋላ ተማሪዎቹ "ስለ ግርማዊት ንግሥት መዝሙር ዘመሩ" (አጽንኦት የታከለ) (ብርሃንና ሰላም፣ ሶስተኛ ዓመት፣ ቁጥር ፴፣ ኀሙስ ሐምሌ ፳፩ ቀን ፲፱፻፲፱)፡፡

## መረጃ ጽሑፎች


መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ (አዘጋጅ አምኃ መርስዔ ኀዘን)። ፪ሺህ። *የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ የዘመን ታሪክ ትዝታዬ ካየሁትና ከሰማሁት 1896-1922*። አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ።

ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል። ፲፱፻፷፮። *ዝክረ ነገር*። አዲስ አበባ፤ ሴንተራል ማተሚያ ቤት።

ባሕሩ ዘውዴ። ፪ሺህ። *የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847 እስከ 1983*። (ተሻሽሎ የታተመ) አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጎ አድራጎት ድርጅት። ፲፱፻፷፫። *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ። ፩ኛ መጽሐፍ*። አዲስ አበባ (?)፤ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት።

ባሕሩ ዘውዴ። ፪ሺህ። የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847 እስከ 1983። (ተሻሽሎ) አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ።

ብርሃኑ ገበየሁ። 1999። *የአማርኛ ሥነግጥም*። አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች።

ተስፋዬ ለማ። 2005። *የኢትዮጵያ ሙዚቃ ታሪክ ከ1889 እስከ 1983 ዓ. ም.* (አርታኢ ዓለማየሁ ገ/ሕይወት)። ዋሽንግተን ዲሲ፣ አሜሪካ።

ታደሰ ሜጫ። ፳፻፬። *ጥቁር አንበሳ በምዕራብ ኢትዮጵያ*። (ለኹለተኛ ጊዜ የታተመ) አዲስ አበባ፤ Eclipse (ኢክሊፕስ አታሚ)።

ትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር። ፲፱፻፷፬። *የተማሪ ቤት መዝሙር*። አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት።

ኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ። 1998። *የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት*። (8ኛ ዕትም) አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን። ፲፱፻፹። *መጽሐፍ ቅዱስ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት*። (የመጀመሪያ ዕትም) አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

ኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ። 2006። *ኣማርኛ መዝገበ ቃላት*። (ሦስተኛ ዕትም) አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ማተሚያ ቤት።

ዘውዴ ረታ። 2006። *ተፈሪ መኰንን ረዥሙ የሥልጣን ጉዞ በምኒልክ፣ በኢያሱና በዘውዲቱ ዘመን፣ ፲፰፻፸፮-፲፱፻፲፬ 1884-1922*። (ሦስተኛ እትም) አዲስ አበባ፤ ሻማ ቡክስ፣ ሲኤምዋይኬ ሚዲያ ኃ.የተ.የግ. ማኅበር።

ዮሐንስ አድማሱ (አዘጋጅ)። ፪ሺህ፩። *ቀኝ ጌታ ዮፍታሔ አጭር የሕይወቱና የጽሑፉ ታሪክ 1887-1939*። (ዮሐንስ አድማሱ 1929-1967) (አሰናኝ ዮናስ አድማሱ) አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ።

ደስታ ተክለ ወልድ። ፲፱፻፷፪። *ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት*። አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ገሪማ ታፈረ። ፲፱፻፺፱። *ጎንደሬው በጋሻው* ። አዲስ አበባ፤ Finfinne Printing and Publishing S. C.

(የደራሲው ስም አልተገለጸም)። ፲፱፻፷፮። *የቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ሽልማት ድርጅት የተሻሻለው ሥርዓተ ቆመት*። አዲስ አበባ፤ (ማተሚያ ቤቱ አልተገለጸም)።

(የደራሲው ስም አልተገለጸም)። ፲፱፻፺፪። *የተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት አጭር ታሪክ*፡ *SHORT HISTORY OF TAFARI MAKONNEN SCHOOL*. አዲስ አበባ? ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

Burrow, J. A. 2008. *THE POETRY OF PRAISE.Cambridge*: Cambridge University Press.

Gebrekidan, Fikru. 2012. "From Adwa to OAU: Ethiopia and the Politics of Pan-Africanism, 1896-1963"; In: *International Journal of Ethiopian Studies*, 2012, vol.6, No. 1/2 (2012), Pp. 71-86.

Mandela, Nelson Rolihlahla. 1994. *LONG WALK TO FREEDOM: The Autobiography of NELSON MANDAELA*. Boston New York Toronto London: Little, Brown and Company.

Nalbandian, Vartkes. 2019. I Want To Die With A Flag: *Ethiopia: My Delusion and Disillusionment*. Independently published.

Simeneh Betreyohannes. 2008. "Music and Politics in Twentieth Century Ethiopia: Empire, Modernization and Revolution" A Thesis Submitted to the School of Graduate Studies of Addis Ababa University in Partial Fulfilment of the Requirements for the Degree of Masters of Arts in Ethiopian Studies, Contemporary Cultural Studies Program.